# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ

አዲስ አበባ መስከረም [illegible] ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ተዘጋጀ


አዘጋጅዎች

ሊቃ ካህናት ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል

መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ

መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን

መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

ሊቀ ሥዩማን ራደ አስረስ



በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ
Printed by Commercial Printing Enterprise

የኮምፒዩተር ለቀማና የገጽ ቅንብር – ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
Computer Typesetting and Design by Ethiopia Book Centre



www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ


ገጽ

የቅዱስ ፓትርያርኩ መልእክት . . . . . . . . . . . . ፮

**ክፍል አንድ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ታሪክ በአጭሩ . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፩

**ክፍል ሁለት**

ገዳማትና ገዳማውያን . . . . . . . . . . . . . . ፳፩

**ክፍል ሦስት**

የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት . . ፴፬

**ክፍል አራት**

ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ . . . . . . . . . . . . ፺፭

**ክፍል አምስት**

የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ . . . . . . ፸፭


www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል አንድ

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ

## ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና

ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት ስለ ነበራት ሃይማኖት ሁለት ዓይነት ታሪክ አለ።

፩ኛ. የኢትዮጵያ አቅኒዎች የመምለኬ እግዚአብሔር የኖህ የልጅ ልጆች ሳባና ሰብታ ቀጥሎም የሴም ወገን ሳባውያን ስለ ነበሩ አያታቸው ኖህ ያመልከው የነበረውን አንድ እግዚአብሔርን ማምለክ አላቋረጡም ነበር። ከዚህም የተነሣ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሳታውቅ የኖረችበት ጊዜ እንደሌለ ታውቋል። ይህንም በትውፊት ያገኘችውን አምልኮተ እግዚአብሔር ጠብቃ ከ፪ሺ፭፻፹፭–፱፻፹፪ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ኖራለች።

፪ኛ. ከ፩ሺ፲፻–፱፻፹፪ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረችው የኢትዮጵያ ንግሥት ማክዳ (ንግሥተ ሳባ) በታሪክ የሰማችውን የሰሎሞንን ጥበብ ለማየትና በዘመኑ የነበረውን የኢትዮጵያን ሥልጣኔ ለማስተዋወቅ የብሉይ ኪዳንንም እምነትና ትምህርት ሥርዓቱንም ከመሠረቱ ለመረዳት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ ምኒልክ የሚባል ልጅ ከሰሎሞን ፀንሳ ተመለሰች። ምኒልክም ተወልዶ ካደገ በኋላ የአባቱን አገር ኢየሩሳሌምን ጐብኝቶ ሲመለስ ጽላተ ሙሴንና ካህናተ ኦሪትን እስከ ሰሎሞን ዘመን ድረስ የተጻፉትን በርካታ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይዞ መጥቶአል።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የአይሁድ እምነት (ተይሀዶ) ከትምህርቱ፣ ከሥርዓተ አምልኮቱና ከመዐርገ ክህነቱ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ገብቶአል።


www.ethiopianorthodox.org

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ወደ ጥንታዊው የኢትዮጵያ ቋንቋ ግእዝ መተተርጐም የተጀመሩት ያንጊዜ ነበር።

ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን እምነትን መቀበልዋን የሚያስረዳ ታሪክ ብቻ አይደለም። እስከ ዛሬ ድረስ በሕዝቡ ዘንድ የሚታዩት የተለያዩ ባህሎችና ትውፊቶችም ዋና ማስረጃዎች ናቸው።

ለምሳሌ:- ኀርመተ መባልዕት

ግዝረት በስምንተኛ ቀን

ሥርዓተ ማኅሌትና መሣሪያዎቹ

ክብረ ታቦትና የበዓላት አከባበር ወዘተ

ከብሉይ ኪዳን የእምነት ሥርዓት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ከዚህም ጋር በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ያላት የቦታ ይዞታ ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ቀድማ የብሉይ ኪዳን እምነት ባለቤት ከሆነችው ከኢየሩሳሌም ጋር የረዥም ጊዜ የእምነትና የታሪክ ግንኙነት እንደነበራት የሚያስረዳ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም ኢትዮጵያ በአንድ አምላክ የምታምን መሆንዋን ደጋግሞ ይናገራል። ስለዚህም ዋናዎቹ ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

«ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» (መዝ.፷፯፥፴፩)

«የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን» (አሞጽ.፱፥፯) «ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል» (ሶፎ.፫፥፲)

ኢትዮጵያ ከ፲፻፹፬፤ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እስከ ፴፬ ዓመተ ምሕረት ድረስ የብሉይ ኪዳንን እምነትና ሥርዓት ጠብቃ ኖራለች።

## ክርስትና በኢትዮጵያ

እግዚአብሔር በነቢያት አድሮ ለሕዝቡ ያናገረው ትንቢት ሁሉ በየጊዜው ተፈጽሞአል። ገና ያልተፈጸመ ቢኖርም እንደሚፈጸም የታመነ ነው። እነሆ «ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» (መዝ.፷፯፥፴፩) ተብሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ኢትዮጵያ በ፴፬ ዓ.ም የክርስትና እምነትን

www.ethiopianorthodox.org

ተቀበለች ይህም የሆነው በሐዋርያት ሥራ ፰፥፳፮–፵ እንደምናነበው የኢትዮጵያ ንግሥት የገርሳሞት(ሕንደኬ) ሙሉ ባለሥልጣን ቀደም ብሎ በተቀበለው የብሉይ ኪዳን እምነት መሠረት በዓለ ፋሲካን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሳለ በወንጌላዊው በፊልጶስ ትምህርት አምኖ በተጠመቀ ጊዜ ነው።

ጃንደረባው ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ከቅዱስ ፊልጶስ ስለ ክርስቶስ የሰማውንና የተረዳውን ለወገኖቹ ለኢትዮጵያውያን እንዳስተማረ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ የሚከተለውን ጽፎአል «የኢትዮጵያ ንግሥት ባለሥልጣን ምሥጢረ ቃለ እግዚአብሔርን ከወንጌላዊው ከፊልጶስ ተምሮ ያመነ፣ አይሁዳውያን ካልሆኑ ወገኖች የመጀመሪያው የክርስትና እምነት ፍሬ ነው። ለወገኖቹም የመጀመሪያው ሰባኪ ወንጌል እርሱ ነው፣ በእርሱም አማካኝነት በመዝሙር ፷፯፥፴፩ ላይ ስለ ኢትዮጵያ የተነገረው ትንቢት ተፈጽሟል» (አውሳብዩስ ፪ኛ መጽሐፍ ቁ.፩)።

ከጃንደረባው ቀጥሎም ቅዱሳን ሐዋርያት ማቴዎስ፣ ናትናኤል፣ በርተሎሜዎስና ቶማስ በኖብያና በኢትዮጵያ ቅዱስ ወንጌልን መስበካቸው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች በእነ ሩፊኖስና ሶቅራጥስ ተመስክሮአል።

የክርስትና እምነት ከሥርዓተ ጥምቀቱና ከወንጌል ትምህርቱ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ቢገባም ጳጳስ ባለመኖሩ ሥርዓተ ቁርባንና ሌላውም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሳይፈጸም እስከ ፫፻፴ ዓ.ም ድረስ ቆይቶአል። በ፫፻፴ ዓ.ም በትውልዱ ጢሮሳውያዊ፣ በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የነበረው ቅዱስ ፍሬ ምናጦስ በንጉሡ በኢዛና ፈቃድ ወደ እስክንድርያ ተልኮ በ፳ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ ጵጵስና ተሾሞ ተመለሰ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ በምልዓት መፈጸም ጀመሩ። የክርስትናው ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነ፣ ቀደም ብለው የክርስትናውን እምነትና ትምህርት በሚገባ ለተማሩትና ብቁ ለሆኑት የዲቁናና የቅስና መዓርግ ተሰጣቸው፣ ምኩራባት ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ተለወጡ በየቦታው አብያተ ክርስቲያናት ተሠሩ፣ ወንጌልም በየአውራጃው ተሰበከ። ቅዱሳት መጻሕፍትም ተተረጐሙ።


www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ፍሬምናጦስ በዚህ ሁሉ ሥራው «ከሣቴ ብርሃን ሰላማ» የሚል ቅጽል ተሰጠው ከእርሱም ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመንበረ ጵጵስና ደረጃ ታወቀች።

በ፭ኛው ምእት ዓመት (በ፬፻፹) ከሶርያና ከታናሽ እስያ ዘጠኙ ቅድሳን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ብዙ መንፈሳዊ ተግባርን አከናው ነዋል። ከሥራቸውም ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ:-

- ሥርዓተ ምንኩስናን፣
- ገዳማዊ ሕይወትንና ምናኔን ማስተማር፤
- በቅዱስ ፍሬምናጦስ ጊዜ ያልተተረጐሙ መጻሕፍትን መተርጐም፤
- ገዳማትን በየቦታው ማቋቋም፤
- በከሣቴ ብርሃን ሰላማ ጊዜ የተቋቋመችውን ቤተ ክርስቲያን ማጠናከርና የመሳሰሉት ናቸው።

በዚህም የተቀደሰ ተግባራቸው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ተብለው ይከበራሉ። በስማቸውም ቤተ ክርስቲያን ታንጾላቸዋል።

ከዚህ በኋላ በ፮ኛው ምእት ዓመት (፭፻፭–፭፻፸፩ ዓ.ም) በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ ይህም የታላቁ ሊቅ የቅዱስ ያሬድ መነሣት ነው። ቅዱስ ያሬድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምራ እስካሁን ድረስ የምትጠቀምባቸውን ጸዋትወ ዜማ በ፫ ዓይነት ስልተ ድምጽና እጅግ ባማረ ጣዕመ ዝማሬ ያዘጋጀ እስካሁን ተወዳዳሪ የሌለው የመንፈሳዊ ዜማ ደራሲ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት፣

«አልቦ እምቅድሜሁ
ወአልቦ እምድኅሬሁ
ማኅሌታይ ስብእ ዘከማሁ»

ከእርሱ በፊት፣ ከእርሱም በኋላ እንደ እርሱ ያለ ማኅሌታዊ (የዜማ ሰው) የለም በማለት ያደንቁታል። ቅዱስ ያሬድ ያዘጋጃቸው ፫ ዓይነት ስልተ ድምጽም ግእዝ ዕዝልና አራራይ ናቸው። ዛሬ ማንኛውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚፈጸመው ቅዱስ ያሬድ ባዘጋጀው ዜማ ነው።


www.ethiopianorthodox.org

በዚህ እንዳለ ኢትዮጵያን የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ቤተ ክርስቲያንዋንም ካቶሊክ ለማድረግ፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቃውንትንም ለማጥፋት ከ፲፱፻፳፰–፲፱፻፴፫ ዓ.ም ኢጣሊያ በኢትዮ ጵያ ላይ ወረራ አደረገች። በዚህም ጊዜ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ቅርሳቅርሶች ተቃጠሉ፣ ንዋያተ ቅድስት ተዘረፉ፣ ጳጳሳት፣ ካህናት፣ መነኮሳትና ዲያቆናት ምእመናንም ተገደሉ።

ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን የግፍ ዘመን በትዕግሥት አሳልፋና እንደገና ተደራጅታ ለሕዝቡ አገልግሎቷን ቀጥላለች። ከጠላት ወረራ በኋላም ቀደም ሲል ከተሾሙት አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት መካከል ሦስቱ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ በአንድ ጳጳስ ብቻም ብዙ መንፈሳዊ ተግባርን ማከናወን ስለማይቻል እንደገና ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፵ ዓ.ም ካይሮ ላይ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ ዳግማዊ አንብሮተ እድ አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ተሾሙ። ከሊቀ ጳጳስ ቄርሎስ ግብጻዊ ሞት በኋላም ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው በፓትርያርክ ዮሳብ ዳግማዊ ተሠየሙ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚህ አኳኋን ከኃይል ወደ ኃይል ከዕድገት ወደ ተሻለ እድገት እየተራመደች ቆይታ በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ሰኔ ፳፩ ቀን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ መጀመሪያው ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ። እነሆ ይህ ራስን ችሎ በራስ የመተዳደር መብትና ሥልጣን ሊገኝ የቻለው በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ጥረት በቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ፍላጎትና በእስክንድርያውያንም ስምምነት መሆኑ ምን ጊዜም ታሪክ የማይረሳው ነው።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነጻነትና ዕረፍት አግኝታ በሰላምና በኅድአት ሕዝቡን እያገለገለችና ቅዱስ ወንጌልን እየሰበከች ስትኖር እንደ ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የውስጥ ተቃዋሚ ኃይል ተነሣ ይህም «እግዚአብሔር የለም» ባዩ የደርግ መንግሥት ነበር። በዚህም ጊዜ በኢትዮጵያና በቤተ ክርስቲያንዋ ላይ ብዙ ጥፋት ደርሶአል። የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ቅዱስ ፓትርያርኩ፣


www.ethiopianorthodox.org

ሊቃነ ጳጳሳቱና ካህናቱ ለብዙ ዓመታት በእስር ቤት ተሠቃይተዋል። በመጨረሻም ቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ቴዎፍሎስ በግፍ ተገድለዋል። አሁን ቤተ ክርስቲያናችንን በመምራት ላይ የሚገኙት ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በክርስትና ሃይማኖት ተቀዋሚ በነበረው የደርግ መንግሥት እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሰባት ዓመታት በእስር ቤት ከባድ ገድል የፈጸሙ ናቸው።

«እናት ልጅዋን ትረሳለችን? ከማኅፀንዋ ለወለደችውስ አትራራምን ምናልባት እናት ይህን ብትረሳ ጽዮን ሆይ እኔ አንችን አልረሳሽም አለ እግዚአብሔር» ተብሎ እንደ ተጻፈ (ኢሳ.፵፱፥፲፭—፲፮) እግዚአብሔር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በመከራው እንድትጠፋ አልተዋትም። በመከራዋም ጊዜ ሁሉ አልረሳትም። ያን ሁሉ የፈተና ጊዜ አሳልፋ ሁሉንም አስተካክላ እግዚአብሔርንም ሕዝቡንም በማገልገል ላይ ትገኛለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ችላ በራስዋ ፓትርያርክ መተዳደር ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ፓትርያርኮችን ሾማለች። በአምስተኛው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ አቡነ ጳውሎስ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ ፓትርያርክና ከምንጊዜውም የበለጠና የተሻለ ዕድገት እየታየ ነው። አዲስ የተሠራው ሕንጻ መንበረ ፓትርያርክና በራስዋ ሊቃውንት በራስዋ የአተረጓጐም ስልት ተዘጋጅቶ የቀረበው ሰማንያ አሐዱ መጻሕፍትን የያዘው ቅዱስ መጽሐፍ በቅዱስነታቸው ዘመን በቤተ ክርስቲያናችን ለሚታየው ዕድገት ዋና ምልክቶች ናቸው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥ ፴፮ አህጉረ ስብከት ያሏት ሲሆን በውጭ ሀገርም በኢየሩሳሌም፣ በካሪቢያን ደሴቶችና በላቲን አሜሪካ፣ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአፍሪካ፣ በካናዳና በሌሎችም አህጉረ ስብከት አሏት። የተከታዮችዋ ምእመናን ቁጥርም ፵ ሚሊዮን ሲሆን ፵ (አርባ) ሊቃነ ጳጳሳት፣ ፬ መቶ ሺህ ካህናት ፴ ሺህ የሰበካ ጉባኤ አብያተ ክርስቲያናት አሏት።

«ይትባረክ እግዚአብሔር ዘአልዐላ ለጽዮን እምዡሉ ዓለማት» ቤተ ክርስቲያንን ከሁሉ ይልቅ ከፍ ከፍ ያደረጋት እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን።



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ሁለት

# ገዳማትና ገዳማውያን በኢትዮጵያ

መጽሐፍ ቅዱሳዊት ኢትዮጵያ ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ በምትከተለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነትና አምልኮ ዕልፍ አእላፍ ሕዝበ ክርስቲያንንና አያሌ የቃል ኪዳን ቅዱሳንን ያፈራች ሀገረ እግዚአብሔር ለመሆን መብቃቷ ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነትና አምልኮ በዚህች አገር ላይ ይህን ያህል ፍሬ ሊሰጥ የቻለውም በሕዝቧ ዕዝነ ልቡና ላይ የተዘራው ቃለ እግዚአብሔር በመልካም ምድር ላይ የወደቀ ዘር ስለሆነ ነው።

በተለይ ደግሞ የአገሪቱን ሕዝብ ከሃይማኖተ ኦሪት ወደ ክርስትና እምነት ያሸጋገረው ቃለ ወንጌል ዜና ከተሰማበት ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመንና እምነቱ በስፋት ከተጠናከረበት ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአገሪቱ ላይ የተነሡትን ቅዱሳን ምእመናን ብዛት በአሐዝ ቀምሮ ለመናገር ባይቻልም በኮከብነት ከሚጠቀሱት አበውና የቃል ኪዳን ቅዱሳን መካከል ጥቂቶቹን ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና የቃል ኪዳን ቅዱሳንና «የሃይማኖት ጋሻ» ለመባል የበቁት አበው የተገኙት ከገዳማውያን መናንያን ብቻ አይደለም። እንደ እነ ሄኖክ፣ ኖህ፣ አብርሃም፣ ሙሴ ወዘተ በዓለም ላይ ሁነው ለዚህ ቅድስናና ብፅዕና የሚያበቃ ገድልና ትሩፋት ከሠሩ የቤተሰብ እና ኅብረተ ሰብእ ኃላፊዎች መናንያን ጭምር ነው። ለኢትዮጵያ ገዳማት ህልውና ዓይነተኛ ምንጭ የሆነውም የእነዚህ ቅዱሳን አበው ህልውና ነው።

ከዚህ ላይ ስለ ኢትዮጵያ ገዳማትና ገዳማውያን አመሠራረትና የኑሮ ሂደት፣ ብዛትና ዓይነት፣ ገዳማቱና ገዳማውያኑ ለአገሪቱ ስለ አበረከቱትና ስለሚያበረክቱት አገልግሎት በቅደም ተከተል ለመግለጽ በቅድሚያ ስለገዳማዊ ሕይወት ጥንተ ታሪክ በአጭሩ ማዘከር አስፈላጊ ይሆናል።

www.ethiopianorthodox.org

«ገዳማዊ» ማለት በተግባራዊ ዘይቤ» የላመ የጣመ ሳይቀምስ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለብስ፣ ጤዛ ልሶ፣ ድንጋይ ተንተርሶ፣ ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሦ፣ ከዓለማዊ ኑሮ ርቆ፣ ከሥጋዊ ግብርና ተድላ ደስታ ተጠብቆ፣ በዕለታዊ ኑሮው ሁሉ ከሰው ሸክምነት ተላቅቆ፣ ራሱን በራሱ እየረዳ ዘወትር በጾምና በጸሎት፣ በገድልና ትሩፋት ተጠምዶ የሚኖር የእግዚአብሔር ሰው» ማለት ነው።

የዚህ ዓይነቱ ገዳማዊ ሕይወት መሥራች በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የተነሣው ግብጻዊ መናኝ አባ እንጦንስ ሲሆን የገዳማውያኑ ኑሮ በቀዋሚ ሕግና ሥነ ሥርዓት እንዲመራ የተደረገው ደግሞ በዚሁ ዘመን በተነሣው ግብጻዊ መናኝ አባ ጳኩሚስ ነው። ስለ ሆነም ገዳማዊው ሕይወትና ቀኖና አሁን ያለው ይዘትና ቅርጽ እንዲኖረው የተደረገው በእነዚሁ ሁለት አንጋፋ አበው መሆኑ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እምነት ነው። ይህ ከሆነ ዘንድ እነዚህን አበው የዚህ ታሪክ መነሻ አድርጎ መናገር ግዴታ ቢሆንም ከእነዚህ ገዳማውያን አበው በፊትም ቢሆን «የዋሕ ጳውሊ» የተባለ ሌላ መናኝ ይህ ዓይነቱን የበረሃ ኑሮ ያኪያሂድ እንደ ነበር ታሪክ ያረጋግጣል።

በገዳም ሕግና ሥርዓት ወንዶችና ሴቶች መናንያን በአንድ ገዳም የጋርዮሽ ኑሮ እንዲኖሩ አይፈቀድም። በመሆኑም የወንዶች መናንያን ገዳም ከላይ ስማቸው በተጠቀሰው አበው በተቋቋመበት ወቅት የሴቶች ገዳምም ለመጀመሪያ ጊዜ ማርያም በተባለች በአባ ጳኩሚስ እኅት እንደ ተቋቋመ ይታመናል። ከእነዚህ አበው በኋላ ገዳማዊ ምናኔ የመላውን የክርስትና ዓለም ትኩረት ስለሳበ በቅጽበት በዓለም ላይ እየተስፋፋ ሄደ። ይህን ትውፊት ከተቀበሉት የክርስትና አህጉርም አንዷዋ ኢትዮጵያ ናት።

## ፪.ሀ.የገዳማት አመሠራረት በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት ባለቤት እንደ ሆነች ሁሉ አያሌ ገዳማትም የሚገኙባት አገር ናት። የእነዚህ ገዳማት ምሥረታ ሂደት የተጀመረውም በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ከሶርያ ግብጽና ከሌላውም የግሪኮ- ሮማን ግዛት በመጡ ዘጠኝ ቅዱሳን ነው። በአሁኑ ጊዜ «ተሥዓቱ ቅዱሳን» እየተባሉ የሚጠሩትም እነዚህ አበው ናቸው። ቅዱሳኑ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በአርዮስ ኑፋቄ


www.ethiopianorthodox.org

ምክንያት ከተፈጠረው አደገኛ ሁከት በመሸሽ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ ለመፍለስ የመረጡትም ኢትዮጵያ የአርዮስን ኑፋቄ በጽኑዕ የምትቃወም ነጻ የክርስትና ሀገር የመሆንዋን ዜና በመስማት ነው። ከቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ማረጋገጥ እንደሚቻለውም የእነዚህ ቅዱሳን ስም:-

አባ አሌፍ፤ አባ አረጋዊ፤ አባ ሊቃኖስ፤ አባ አፍጼ፤ አባ ገሪማ፤ አባ ጉባ፤ አባ ይምዓታ፤ አባ ጸንጠሌዋን፤ አባ ጽሕማ ይባላል፤ ከእነዚህ ቅዱሳን ፊትና ኋላም እንደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና አባ ሊባኖስ ያሉ የውጭ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ለገዳማዊ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል። እነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የገዳማዊ ኑሮ መሠረት በመጣሉ በገዳማቱ መመሥረት የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ሕይወት ትናንት የነበረውንና ዛሬም ያለውን ስፋትና ጥልቀት እንዲያገኝ አድርጐታል። ይኸውም ገዳማዊ ሕይወት ለዓለማዊ ክብርና ብልጽግና ሲሉ ሰብአዊ ተፈጥሮን በዝርፊያና በንጥቂያ፤ በግፍዕና አመጽ ተግባር ለሚያዋርዱ ዓለማውያን ወገኖች የሚሰጠው ትምህርት ከፍተኛ በመሆኑ ነው።

## ፪.፩. የገዳማዊ ኑሮ ሂደት በኢትዮጵያ

ገዳማዊ ኑሮ በሁለት ይከፈላል። ይኸውም አንደኛው ክፍል የአንድነት ገዳም ሲባል ሁለተኛው ደግሞ የቆሪት ገዳም ይባላል። የአንድነት ገዳም የሚባለው በአንድነት ሠርቶ በአንድነት መመገብ፤ በአንድነት መጸለይና ገዳማዊ አገልግሎትን በኅብረት መፈጸም የሚቻልበት ገዳም ነው።

በዚህ ዓይነቱ ገዳም ምንም ዓይነት የግል ንብረት ይዞታ አይፈቀድም፤ ያለጸሎትና ተግባር ሥራ ፈት ሁኖ መቀመጥም በጥብቅ የተከለከለ ነው። ያለ በቂ ምክንያትና ያለ ገዳሙ ማኅበር ፈቃድ ከገዳሙ ወጥቶ መዘዋወርም አይፈቀድም። አመጋገብንም በሚመለከት የገዳሙ ቀኖና የሚፈቅደውን የምግብ ዓይነትና መጠን ተላልፎ መመገብ ክልክል ነው። በሞት ለሚለይ የገዳሙ አባል ማልቀስና ማዘን፤ በሥራ መለገም፤ ስሕተትን መደበቅ፤ በጠቅላላ የዓለማዊና ሥጋዊ ፍላጐት ተገዥ መሆን የገዳማዊ ሕይወት ገጸ ባሕርይ አይደለም። ከመገልገል ይልቅ ለማገልገል መፋጠንም የገዳማዊ ኑሮ ሌላው ግዴታ ነው። ከዚህ ጋር ገዳም የሥራ እንጂ የስንፍ መጠሪያ ቦታ ባለመሆኑ ማንኛውም ገዳም የሚተዳደረው

www.ethiopianorthodox.org

ገዳማውያኑ ሠርተው በሚያገኙት ገቢ ነው። ሥራ አለ መፍታቱም ራሱ የምናኔ ሕይወት ሌላው ገጽታ ሲሆን ሥራ ፈትነት ደግሞ የዚህ ተቃራኒ የሆነ ኢገዳማዊ ጠባይ ስለ ሆነ በእርጅና ወይም በሕመም ምክንያት ለመሥራት የማይችል አቅመ ደካማ ካልሆነ በቀር በተረጅነት እንዲኖር የሚፈቅድም ሆነ የሚፈቀድለት ገዳማዊ የለም። አቅመ ደካማ እንኳ ቢሆን ማኅበሩ ድካሙን አይቶ ከሥራ ነጻ እንዲሆን ካላደረገው በቀር እሱ ራሱ ደክሚያለሁ ልረፍ ብሎ አያርፍም፤ ልረፍ ብሎም አይጠይቅም።

በመሠረቱ የአንድነት ገዳም ማለት በአጭሩ የመናንያን የጋርዮሽ ኑሮ ተቋም ማለት ቢሆንም ከመናንያኑ መካከል ከመንፈሳዊ ሕይወት ምልዓተ ደረጃ ላይ የደረሱ ገዳማውያን በገዳሙ ማኅበር ፈቃድና ቡራኬ ከገዳሙ አንድነት ሳይለዩ በልዩ ቦታ ተወስነው የተባሕትዎ (የብቸኝነት) ኑሮ መኖር ይችላሉ። እነዚህ ዓይነቱ መናንያን ታዲያ የተባሕትዎ ኑሮ የሚያስከትለውን ፈተና ሁሉ መቋቋም የሚችሉበት መንፈሳዊ ብቃት ስላላቸው ለከፋ መንፈስ የተጋለጡ አይሆኑም።

ይህ እንዲህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከፍራፍሬና ከሥራ ሥር በቀር ሌላ እህል የማይቀመስባቸው የምናኔ ቦታዎች መኖራቸውን ሳይጠቅሱ ማለፍ ስለ ኢትዮጵያ ገዳማት ጠቅላላ የምናኔ ሕይወት ለመግለጽ የተደረገውን ጥረት የተሟላ አያደርገውም።

የቁሪት ገዳም — በመባል የሚጠራው ገዳም ከአንድነት ገዳም የሚለየው በዚህ ገዳም የተወሰነ የግል ንብረት ይዞታ የሚፈቀድ በመሆኑ ብቻ ነው። ከዚህ በቀር የገዳማውያኑን የምናኔ ጠባይ በሚመለከት ያንዱ ከሌላው ያልተለየ ስለ ሆነ ስለቁሪት ገዳም ሊነገር የሚችል ልዩ ታሪክ የለም።

ስለ ኢትዮጵያውያን የምናኔ ሕይወት ታሪክ በሚነገርበት ጊዜ ሌላም ሳይጠቀስ የማይታለፍ ዓቢይ ነገር አለ። ይህም ከአንድነት ገዳማት ርቀው በሚገኙ አንዳንድ ጫካዎችና ዋሻዎች እንደ መልከ ጼዴቅና እንደ ዮሐንስ መጥምቅ የተለየ አለባበስና አስፈሪ ግርማ ሞገስ ያላቸው ባሕታውያን የሚከሠቱበት ጊዜ መኖሩ ነው። እነዚህ ዓይነቱ ባሕታውያን በኅብረተ ሰቡ አጠራር «ግሑሳን» ይባላሉ።

«ግሑስ» ማለትም «ከሰው ርቆ የሚኖር ስውር ባሕታዊ» ማለት ነው።


www.ethiopianorthodox.org

| ስም | የተነሡበት ክፍለ ዘመን |
|---|---|
| አቡነ ሐደራ | |
| አቡነ ሐራ | |
| አቡነ ሕንፃ ሃይማኖት | በ፲፬ኛው ክፍል ዘመን |
| አቡነ ኂሩት | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ሕፃን ሞዓ | በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ኢያሱ | በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ክርስቶስ ቤዛነ | |
| አቡነ ልብጽዮስ | |
| አቡነ መባ ማርያም | |
| አቡነ መባአ ሥላሴ | |
| አቡነ መባአ ጽዮን (ተ.ማ) | |
| አቡነ መድኀኒነ እግዚእ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ማዕተበ እግዚእ | |
| አቡነ መልከአ ክርስቶስ | |
| አቡነ መልከጼዴቅ ዘመርሐቤቴ | |
| አቡነ መልከጼዴቅ ዘዳግና | |
| አቡነ ማማስ | |
| አቡነ መርዓዊ ክርስቶስ | |
| አቡነ መርሐ ኢየሱስ | ፩ሺ፬፻፯–፩ሺ፬፻፶፯ |
| አቡነ መርቆሬዎስ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ማርቆስ | |
| አቡነ መስቀል ቤዛነ | |
| አቡነ ማትያስ ዘጉጃም | |
| አቡነ ማትያስ ዘሸማግሌ | በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ መዝሙረ ድንግል | በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ መዝሙረ ክርስቶስ | |
| አቡነ መዝራዕተ ክርስቶስ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ሙሴ (የካሌብ ወንድም) | በ፯ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ሙሴ ጸሊም (በግብጽ የኖረ) | |
| አቡነ ንዋየ ኢየሱስ | |
| አቡነ ኖላዊ | |
| አቡነ ኖላዊነ ኄር | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ጳውሎስ ዘደ ሊባኖስ | በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ጳውሎስ ዘተንቤን | |



www.ethiopianorthodox.org

| ስም | የተነሡበት ክፍለ ዘመን |
| --- | --- |
| አቡነ ዮሐንስ ዘበንኮል | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዮሐንስ ዘቢዘን | በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዮሐንስ ዘጉናንቁ | |
| አቡነ ዮሐንስ ከማ ዘአገድ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዮሐንስ ዘጽላሉ | |
| አቡነ ዮሐኒ ዘደብረ ዓሣ | |
| አቡነ ዮናስ | በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዮሐንስ ዘቈፋት | በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዮሴፍ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዮስጦስ | በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዘኢየሱስ | በ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዘካርያስ ዘገሊላ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዘካርያስ ዘጊፋ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዘካርያስ ዘበርበር | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዜና ማርቆስ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዘሊባኖስ | |
| አቡነ ዘመድኅን | |
| አቡነ ዘርዐ አብርሃም | በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን |
| አቡነ ዘርዐ ቡሩክ | |
| አቡነ ዘርዐ እንድርያስ | |
| አቡነ ዘርዐ ሙሴ | |
| አቡነ ዘዮሐንስ | በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን |
| ቅድስት እኅተ ክርስቶስ | በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን |
| ቅድስት እኅተ ጴጥሮስ | በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን |
| ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ | |
| ቅድስት መክብበ ድንግል | |
| ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ | |
| ቅድስት መስቀል ክብራ | በ፲፪ኛው ክፍለ ዘመን |
| ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ | በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን |
| ቅድስት ወለተ ማርያም | |
| ቅድስት ዜና ማርያም | |

ከእነዚህ ቅዱሳን መካከል አንዳንዶቹ ምናኔን ከሐዋርያነትና ከሰማዕትነት እንዲሁም ከማኅበራዊ አገልግሎት ጋር በማጣመር፣ ሌሎች

www.ethiopianorthodox.org

ደግሞ በገዳማዊ ኑሮ ብቻ ራሳቸውን ከዓለም ፈጽሞ በማግለል በፈጸሙት ገድልና ትሩፋት የቃል ኪዳን ቅዱሳን ለመሆን የበቁ ቅዱሳን ናቸው። በመሆኑም አብዛኛዎቹ በስማቸው ቤተ ክርስቲያን የታነጸላቸውና ገድል የተጻፈላቸው ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ ስማቸውና ገድላቸው በስንክሳር ብቻ የሚዘከር ቅዱሳን ናቸው።

በኢትዮጵያ የገዳማትና ገዳማውያን ህልውና ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ የምናኔ ሕይወት የብዙዎችን ትኩረት የሳበ ልዩ ሕይወት ስለ ሆነ ነገሥታት ሳይቀር ቤታቸውንና ቤተ መንግሥታቸውን እንደ ገዳም አድርገው የምናኔ ኑሮ በመኖር ለቅድስና የበቁ ብዙዎች ናቸው።

ቤታቸውንና ቤተ መንግሥታቸውን እንደ ገዳም አድርገው ማለት ገዳም ሳይገቡ በአሉበት ቦታ ሥውር መናንያን ሁነው ለቅድስና የበቁና በስማቸውም ቤተ ክርስቲያን የታነጸላቸው መናንያን ነገሥታት:-

| ስም | የተነሡበት ክፍለ ዘመን |
|---|---|
| ቅዱስ አብርሃ | በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን |
| ቅዱስ አጽብሐ | በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን |
| ቅዱስ ላሊበላ | |
| ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ | በ፲፪ኛው ክፍለ ዘመን |
| ቅዱስ ገብረ ማርያም | በ፲፪ኛው ክፍለ ዘመን |
| ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ | በ፲፪ኛው ክፍለ ዘመን |
| ቅዱስ ጻድቁ ዮሐንስ | በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን ወዘተ. |

ሲሆኑ እንደ አጼ ካሊብ፣ አጼ ገብረ መስቀል፣ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ፣ አጼ ናዖድ ወዘተ ያሉት ነገሥታት ደግሞ በመንፈሳዊነታቸው ለሚመሩት ሕዝበ ክርስቲያን መልካም ምሳሌና የክርስትና እምነት ጋሻዎች በመሆን የኖሩ ደጋግ ነገሥታት ናቸው።

## ሐተታ

ሀ. አብርሃና አጽብሐ ከሕጽዋ ለሕንደኬ ቀጥሎ የክርስትና እምነትን የተቀበሉና ያስፋፉ በዘመናቸው የተነሣው የአርዮስ ኑፋቄ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገባ የተከላከሉና የተቃወሙ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም በኩል ኢገዳማውያን መናንያን ሁነው የኖሩ ቅዱሳን ነበሩ። እንዚህ መሪዎች በእርግጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ክርስቲያን

www.ethiopianorthodox.org

ነገሥታት ነበሩ። በመሆኑም የአርዮስ ኑፋቄ ደጋፊ የነበረው የታላቁ ቆስጠንጢኖስ ልጅ ኮንስታንቲዮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንንም የአርዮስ ኑፋቄ ደጋፊ ለማድረግ ያልተሳካ የተማኅጽኖ ደብዳቤ የጻፈው ለእነዚህ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ነገሥታት ነበር። ጥያቄውን ላለመቀበል ነገሥታቱ በወሰዱት አቋም የተደሰተው ቅዱስ አትናቴዎስ ለእነዚህ ነገሥታት የምስጋና ደብዳቤ መጻፉም ታውቋል።

ለ. ቅዱስ ላሊበላ፣ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ ገብረ ማርያም፣ ነአኩቶ ለአብ፣ ጻድቁ ዮሐንስ እንደ እውነተኛ የእግዚአብሔር መጋቢ ለሕዝባቸው ፈታሒ በጽድቅ ኮናኒ፣ በርትዕ እንደ ሐዋርያ የክርስትና እምነት መስካሪና አስተማሪ፣ እንደ አንድ ገዳማዊ ዓለማዊ ኑሮን መናኝ፣ የሕዝብ ቸር እረኛ፣ ሰውንና እግዚአብሔርን አፍቃሪ ወዘተ. የሆኑ የእግዚአብሔር መሢሆች በመሆናቸው በስማቸው ቤተ ክርስቲያን የታነጸላቸውና ገድል የተጻፈላቸው ቅዱሳን ነገሥታት ለመሆን በቅተዋል።

ከዚህም ጋር ቅዱስ ላሊበላ በአሁኑ ጊዜ ለዓለም ብርቅና ድንቅ ቅርሶች ሁነው የተገኙትን ከቋጥኝ የተፈለፈሉ አብያተ ክርስቲያናትን ያሠራ ቅዱስ ንጉሥ ነው። ጻድቁ ዮሐንስም ከላይ ከተገለጸው የቅድስና ተግባር ጋር ከሕዝብ የተሰበሰበ ገንዘብ ላለመጠቀም በመወሰን በራሱ ተግባረ ዕድ ራሱን ሲረዳ የኖረ መናኝ ንጉሥ ነበር። የሕዝብ አቤቱታ ማሰሚያ ደወል በአደባባይ በመትከልና ፍርድ የጐደለበት ሁሉ ይህን የደወል ድምጽ በማሰማት በቀጥታ ወደራሱ እየቀረበ ፍርድ እንዲያገኝ ማድረግም የዚህ ንጉሥ የታወቀ በጐ ተግባር ነበር። በዚህ ሁሉ ምክንያት ንጉሡ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሕዝብ ዘንድ ጻድቁ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል።

ሐ. አጼ ካሌብ በ፮ኛው ክፍለ ዘመን በስማቸው ቤተ ክርስቲያን ከታነጸላቸው ቅዱሳን ነጋሥያን አንዱ ባይሆንም ከእነዚያ ባላነሰ ደረጃ ስሙ የሚዘከር መንፈሳዊ ነጋሢ ነበር። ለዚህ ታላቅ ክብር የበቃውም እንደኛ ፊንሐስ የተባለ አይሁዳዊ በየመን በሚገኙ ክርስቲያኖች ላይ


www.ethiopianorthodox.org

ከፍተኛ ዕልቂትን ባደረሰ ጊዜ በቁስጥንጥንያው ክርስቲያናዊ ንጉሥ ዩስጢኖስና በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ጢሞቴዎስ ፫ኛ ጥያቄና በራሱም ተነሳሽነት ወደ የመን ዘምቶ የመስቀል ጦርነት በማድረግ ቀንደኛውን የክርስትና እምነት ጠላት ድል አድርጐ ክርስቲያኖችን ነጻ በማውጣቱ፣ ሁለተኛ ከዚህ የሰማዕትነት ገድል በኋላም መንግሥቱን ትቶ ገዳም የገባ መናኝ የእግዚአብሔር ሰው በመሆኑ ነው።

መ. አጼ ዘርዐ ያዕቆብም (በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን) እንዲሁ የክርስትና እምነትን በማስፋፋትና በማጠናከር በፈጸመው ታላቅ ተግባር «ቆስጠንጢኖስ» ተብሎ የተሰየመ፣ በመንግሥት ላይ በነበረበት ጊዜም ከገዳማዊ ኑሮ ጋር ተነጻጻሪ የሆነ መንፈሳዊነት የነበረውና በኋላም መንፈሳዊ ፍላጐቱን ለማርካት ወደ ገዳም የምናኔ ጉዞ ያደረገ ክርስቲያን ነጋሢ በመሆኑ እንደእነ ካሌብ ስሙ በመንፈሳዊ ስሜት ሲዘከር የሚኖር ንጉሥ ሁኗል።

ከዚህ ጋር አያሌ መጻሕፍት ከውጭ ቋንቋ ወደ ግዕዝ የተተረጐሙትና አያሌ ድርሳናት የተደረሱት በዚህ ነጋሢ ዘመን ስለ ሆነ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ታላቅ ቦታ ያለው ደግ ንጉሥ ነው። የዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ሕይወት የነበራቸው ነገሥታት እነዚህ ብቻ አይደሉም። ብዙዎች ናቸው፣ ይህ የሆነው ታዲያ በክርስትና እምነት ጥንካሬ ስለ ሆነ ከገዳማት ምሥረታ በኋላ በሁሉም ዓይነት የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያናዊ ሕይወት የቱን ያህል ስፋትና ጥልቀት ያለው ሊሆን እንደቻለ መገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም።

## ፪.መ ገዳማት ለኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የሚያበረክቱት አገልግሎት

ገዳማት የምናኔ ቦታዎች ቢሆኑም ለአገሪቱና ለኅብረተ ሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት በጸሎት ብቻ የተወሰነ አይደለም፣ ከዚህ ጋር ለኅብረተ ሰቡ የቀለም፣ የዜማ፣ የትርጓሜ መጻሕፍት፣ የቅርጻቅርጽና ሥዕላ ሥዕል ሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት፣ የቅርሳቅርስ ቤተ መዘክርና ቤተ መጻሕፍት ወዘተ በመሆን ለአገሪቱ ሰፊ አገልግሎት ሲሰጡ የኖሩና


www.ethiopianorthodox.org

ያሉ በመሆናቸው የገዳማቱ መኖር ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጠው ጥቅም በዋጋ ሊተመን የሚችል አይደለም። በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱን በመምራት ላይ የሚገኙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የተገኙትም ከእነዚህ ገዳማት በአንዱ ነው።

የገዳማቱን ብዛት በሚመለከት በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱ ካሏት ሠላሳ አምስት ሺህ ያህል የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ከሺህ በላይ የሚሆኑት ገዳማት ናቸው። ከእነዚህ ገዳማት መካከል አብዛኞዎቹ የወንድ ገዳማት ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ የሴት ገዳማት ናቸው። ከ፩ሺ፱፻፸፯–፸፰ ዓ.ም ባለው ጊዜ በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል ላይ ደርሶ በነበረው ድርቅና ረሃብ በርከት ያሉ ገዳማትም የድርቁ ተጠቂ ሆነው ስለ ነበር የካናዳ አብያተ ክርስቲያናት ለእነዚህ ገዳማት ምን ጊዜም ሲዘከር የሚኖር ርዳታ አድርገዋል። አስቀድሞ እንደተገለጠው እነዚህ ገዳማት የምናኔ ቦታዎች ብቻ ሳይሆኑ የአገሪቱ ታሪክ አብያተ መዘክርም በመሆናቸው ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ለእነዚህ ገዳማት ደኅንነት መጠበቅም ሆነ በጠቅላላ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድገትና ጥንካሬ የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ነው።


www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት

ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሀገር እንደ መሆኑዋ ጥንታዊ የሆነ ራሱን የቻለ ኢትዮጵያዊም የሆነውን ሁሉ የሚያኮራ ልዩ ጥናትንም የሚጠይቅ የራሱ የሆነ ጥንታዊና ብሔራዊ ሥርዓተ ትምህርት አላት።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ኦሪት ድኅረ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ወንጌል ያመነች ጥንታዊት ሀገር ከመሆኑዋም በላይ በዚያው የዘመን ርዝመት መጠንም በሥነ ጽሕፈት የታወቀችና የሕዝቡዋ ሥልጣኔ፣ ጀግንነቱ፣ እምነቱና ባሕሉ ሌላውም ሁሉ እንዴት እንደ ሆነ ሊታወቅ የቻለው መጀመሪያ በሐውልቶች በጠፍጣፋ ድንጋዮችና በሸክላ ዕቃዎች ላይ በኋላም በብራና ተጽፈውና ተሥለው ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ በመጡት የቅርጻ ቅርጽ፣ የጽሑፍና የሥዕል ቅርሶች ነው። ይህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመናት የትምህርት ማዕከል ሆና ኅብረተ ሰቡን ስታገለግል ከመኖሩዋ የተነሣ ለሀገሪቱ ያተረፈችው የሥልጣኔ ውጤት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። በሀገራችን ትምህርትና ሥነ ጽሕፈት የተጀመረው ከጥንት ዘመን ጀምሮ ለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎች ይገኛሉ።

ለምሳሌ ያህል በአክሱም ሐውልቶች ላይ በሳባውያን፣ በግሪክና በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉት ጽሑፎች የዓይን ምስክሮች ናቸው።

የገናናው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት የኢዛና ታሪክም በአክሱም ሐውልቶች ላይ በግዕዝ ቋንቋ ተጽፎ ይገኛል።

በሐውልቱ ላይ የሰፈሩት ቁም ነገሮችም ንጉሡ ስለ ፈጸማቸው ተጋድሎዎችና ስለ ተቀዳጃቸው ድሎች የሀገሪቱን ግዛት ለማስፋፋት የተደረገውን እንቅስቃሴና ሕዝቡ ለአምላኩ ያቀርብ የነበረውን ምሥጋና ያንጸባርቃል። በአክሱም መንግሥት ከላይ በተጠቀሰው ዓለም ዐቀፍና


www.ethiopianorthodox.org

ብሔር ዐቀፍ ቋንቋዎች ትምህርትና ሥነ ጽሕፈት የዳበረ ስለ ነበር ሀገሪቱ የአንድ ቋንቋ ባለቤት ብቻ እንደ አልነበረች መገመት ይቻላል።

በግብረ ሐዋርያት ም.፰፥፳፮ ላይ እንደ ተመዘገበው የንግሥት ሕንደኬ መልእክተኛ የነበረው ጃንደረባ ለጸሎት ወደ ኢየሩሳሌም ሔዶ በነበረበት ወቅት በሠረገላ እየተጓዘ ሳለ መጽሐፈ ኢሳይያስን በግዕዝ ቋንቋ ሲያነብ መገኘቱ ተጽፎዋል፤ ይህም ሁኔታ በሀገራችን ከጥንት ጀምሮ የማንበብና የመጻፍ ትምህርት ተስፋፍቶ እንደ ነበረ የሚያስረዳ ነው። ሆኖም የትምህርት መሠረት የሆነው ፊደልና የሥነ ጽሕፈት ስልት በመላ ኢትዮጵያ የተስፋፋው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት በኢትዮጵያ መስፋፋት ከጀመረበት ዘመን አንሥቶ መሆኑ ግልጽ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአራተኛው መቶ ዓመት (፫፻፴ ዓ.ም) ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ሆና ከተቋቋመችበት ጊዜ ጀምሮ ትምህርትን በኃላፊነት ስትመራ ኑራለች። በተለይም የመጀመሪያው ጳጳስ ሆኖ የተሾመው ፍሬምናጦስ በኋላ ከሣቴ ብርሃን ሰላማ የተሰኘው ቀደም ብሎ ሲሠራበት የቆየውን ፊደል እንዲሻሻል ከማድረጉም በላይ አያሌ መጻሕፍትን ከጽርዕና ከዕብራይስጢ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ ቋንቋ እንዲተረጐሙ አድርጎአል።

ለግዕዝ ፊደላት መልክና ቅርጽን በመስጠት የሥነ ጽሕፈት እውቀት እንዲስፋፋ ያደረጉት በአክሱም ዘመነ መንግሥት የነበሩት የቤተ ክህነት ሊቃውንት መሆናቸው የታወቀ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያ ሀገራችን የራስዋ የሆነ ፊደልና ትምህርት ባለቤት እንድትሆን በማድረግዋ ለሀገሪቱና ለሕዝቡ ሥልጣኔ እድገት ያበረከተችው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶታል። በአፍሪቃ አህጉር ከሚገኙት ሀገሮች ሁሉ ከቀድሞ ጀምሮ የራስዋ ፊደል የነበራትና የአላት ኢትዮጵያ ብቻ በመሆንዋ በቤተ ክርስቲያኒቱ በተገኘው በረከትና ጸጋ መላው የሀገሪቱ ሕዝብ ሲመካበት ይኖራል።

ለማንኛውም ትምህርት፣ ሥነ ጽሕፈትና ቋንቋ መሠረቱ ፊደል ስለ ሆነና መሠረታዊ ቋንቋ ታሪካዊ ተብሎ ሊሠየም የሚችለውም ፊደል ተቀርጾለት የሥነ ጽሕፈት መሠረት በመሆን ማንኛውም ነገር ለትውልደ ትውልድ በጽሑፍ ተላልፎ ሲገኝ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ምንጭ እንደ መሆንዋ መጠን ለሀገሪቱ ቋንቋዎች መሠረት የሆነውን ጥንትም ሆነ አሁን የምንገለገልባቸውን ፊደላት ቀርጻና መልክ ሰጥታ ሕዝቡ እንዲጠቀምበት ሥነ ጽሕፈት እንዲስፋፋበት፣ ታሪክ እንዲመዘገብበት፣ ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት እንዲገለገሉበት ማድረግዋ ለሀገሪቱና ለሕዝቡ ያላትን በአለውለታነት የበለጠ ገናና ያደርገዋል። ብዙው የዓለም ክፍል ገና በጨለማ ውስጥ በነበረበትና የእውቀት ብልጭታ በአልፈነጠቀበት፣ እንደ አሁኑ ሁሉ የሕትመት መኪና ከመፈልሰፉ በፊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ከበግና ከፍየል ቆዳ ብራና አውጥተው ራምመው ዳምጠው አፍፈውና ከፍፈው እንደ ዛሬው ወረቀት በመስመርና በጎዳግ በግሌትና በዓምድ አስምረው አዘጋጅተው ቀለሙንም ከልዩ ልዩ የቤት ዕቃዎች ጥላሸቶችን በመሰብሰብ ከተለያዩ ዕጸዋት ቅጠሎችን እያሳረሩ ደቁሰው ከእህል ሐሩርና ከሙጫ ጋር ቀላቅለው በማሸትና በማዋሐድ ደንበኛ የሆነና ዛሬ ለሕትመት አገልግሎት ብቁ ናቸው ተብለው ከሚታመንባቸው የቀለም ዓይነቶች የማያንሱ የተለያዩ ቀለማትን በመቀመም በሸምበቆ (መቃ) ብርዕ ቀርጸው በጉልህ ወይም በረቂቅ ለመጻፍ በሚያስችል ሁኔታ በሚፈልጉት ዓይነት እያዘጋጁ ከፊደል ጀምሮ ያሉትን ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያንና የሀገር ታሪክ ሌሎችንም መጻሕፍት በየደረጃቸው በቁም ጽሕፈት ጽፈው በሚፈልጉት ቅርጽ ያዘጋጃሉ ቀጥሎም ከዘመናዊው የአጠራረዝ ስልት በማያንስ ሁኔታ እየጠረዙና እየደጐሱ ለተጠቃሚው ሕዝብ ያቀርባሉ በዚህ ሁኔታ አሁን እስከ አለንበት ዘመን ድረስ ያበረከቱት የትምህርትና የሥነ ጽሕፈት ጥበብ ከፍተኛ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኔ ዕድገት አኩሪ ታሪክ ነው።

የጥንቱ የብራና መጻሕፍት ገበታቸው ከዕንጨት ውስጣቸው ከብራና የተዘጋጁ ስለሚሆኑ ከጠንካራነታቸው የተነሣ በሺ ዓመታት የሚቆጠሩ ዘመናት ያሳለፉ በጥንካሬያቸው ወደር የሌላቸው በመጠን ትላልቅ የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትና የታሪክ መጻሕፍት በአድባራትና ገዳማት ስለሚገኙ የጥንቱን የሥነ ጽሕፈት ዕድገት በዚህ መለካት ይቻላል አሁንም ሀገሪቱ ተወዳዳሪ የሌላቸው የብዙ ታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት ሆና ልትገኝ የቻለችው በጽሑፍና በሥዕል (አርት) ከታወቁት በሥልጣኔ ከገፉት ቀደምት ሀገሮች አንደኛ ለመሆን የበቃችው በኢትዮጵያ


www.ethiopianorthodox.org

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ከፍተኛ ጥረትና ድካም ነው።

ሕዝቡም የዚህ ሥነ ጥበብ ተካፋይ በመሆን በሀገሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በባህሉና በታሪኩ ሲኮራ ይኖር ዘንድ ታላቅ ዕድል አጋጥሞታል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ብራና አውጥተው ቀለም አሽተው ብርዕ ቀርጸው ዓይናቸው እስከሚፈዝ ጉልበታቸው እስከሚደነዝዝ የጻፏዋቸው የእምነት የቀኖና የሥነ ምግባር፣ የታሪክ መጻሕፍት ጉልቄ መሳፍርት የላቸውም።

እነዚህ መጻሕፍት በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙ ሲሆን ብዙዎቹ በሕገ ወጥ መንገድ ከሀገር ውጭ ወጥተው በተለያዩ አህጉር ዩኒቨርሲቲዎችና ቤተ መዘክሮች ይገኛሉ። መጻሕፍቱ ከቀድሞ ጀምሮ የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪክ የሥልጣኔ እድገት በጉልህ እያስረዱ ቢሆንም በሕገ ወጥ መንገድ ወጥተው በባዕድ ሀገር መቅረታቸው እጅግ ያሳዝናል።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በየዘመኑ ማይምነትን ስትዋጋ ከኖረችባቸው ዘዴዎች አንዱ የሥነ ጽሕፈት ጥበብ ነው። ምክንያቱም ገዳማቱንና አድባራቱን የትምህርት ማዕከል በማድረግ ከመንፈሳዊው ትምህርት ጋር መሠረታዊ የሆነውን የንባብና የሥነ ጽሕፈት ትምህርትን አጣምራ ስትሰጥ የኖረች በመሆንዋ ነው።

ይህም በአለፉት ዘመናት ይፈጸም የነበረ ብቻ ሳይሆን አሁንም ያለማቋረጥ ሲሠራበትና ሲካሄድ የሚታይ ተግባር ነው።

በሀገራችን የዘመናዊውን ትምህርት አሁን በመምራት ላይ የሚገኘው የትምህርት ሚኒስቴር ከመቋቋሙ በፊት ለሦስት ሺህ ዘመናት ያህል ትምህርቱ ይካሔድ የነበረው በቤተ ክህነት እንደ ነበር ታሪክ ይመሰክራል። ሊቃውንቱና ካህናቱ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ሳይወሰኑ ከሀገር መሪነት እስከ ተራ ሠራተኛነት ያለውን የመንግሥት ሥራ ያካሔዱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ምሁራን እንደ ነበሩ የታወቀ ነው።

ከዚህም ጋር ፍትሐ ነገሥት የተማሩት በዳኝነትና በአስተዳደር አስፈላጊ በሆኑ ሥራዎች ሁሉ በመመደብ የመንግሥቱን ሥራ አመራር እያቃኑ ፍትሕ ርትዕ እንዲሰፍን እያደረጉ ሕዝቡን ሲያገለግሉ


www.ethiopianorthodox.org

ከመኖራቸውም በላይ የሀገሪቱን ነጻነትና ደኅንነት በመጠበቅና በማስጠበቅ ረገድም የሚጠበቅባቸውን ግዳጅ እየተወጡ ለሕዝቡ መልካም አርአያና ምሳሌ ሆነው ኖረዋል።

በ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትምህርት ሚኒስቴር በሀገሪቱ ተቋቁሞ ዘመናዊ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላም ቢሆን የሚኒስቴሩን መ/ቤት በማጠናከርና የትምህርቱን ሂደት በማካሔድ ከፍተኛ ሚና ይጫወቱ የነበሩት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ናቸው። ሊቃውንቱ በየትምህርት ቤቱ ተመድበው ለተማሪዎቹ ከመጀመሪያው መሠረታዊ ትምህርት እስከ ከፍተኛው ደረጃ ከማስተማር ጋር የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ትምህርትን ፍቅረ ሀገርን ለዘመኑ ትውልድ በማሳወቅ በአኃዝ የማይቆጠር አገልግሎት አበርክተዋል።

ዛሬም ቢሆን ዘመናት የማይቆጠርላቸው የሙዓለ ሕጻናት ትምህርት ቤቶች እንደ አሁኑ ከመቋቋማቸው አስቀድሞ ለዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መጋቢዎች ሆነው አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩትና ያሉት እነዚሁ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያኒቱ የንባብ ትምህርት ቤቶች ናቸው።

በመላ ኢትዮጵያ ከ፴፭ ሺህ በላይ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ አብዛኞዎቹ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ያላቸው ናቸው። በዚህም መሠረት አሁንም የነበረው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በጥልቀትና በስፋት እየተሰጠ ይገኛል። መምህራኑም ቀደም ሲል ከነበረው በበለጠ በንቃትና በትጋት እያስተማሩ ነው።

ከንባቡ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር ዘመናዊው ትምህርትም እንዲሰጥ ጥረት እየተደረገ ነው።

በዚህ ዓይነት የተማሪው ቁጥር እጅግ ብዙ ስለሚሆን በቤተ ክርስቲያኒቱ የሚካሔደው መሠረታዊ የሆነው ጥንታዊ ትምህርት እየተስፋፋና እድገት እያሳየ መምጣቱን ስናይ በዚያው አንጻር ማይምነት እየቀነሰ፣ የማያነቡ እንዲያነቡ የማይጽፉት እንዲጽፉ እየተደረገ ነው።

በዚህ መነሻነት ኅብረተሰቡ በተለይም የዘመኑ ትውልድ ስለግኝቱ ማለትም ስለ ፊደል አመጣጥ ብቻ ሳይሆን ስለ አስገኝዋ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውለታ ብዙ ያውቃል፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምራቸው የትምህርት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው።


www.ethiopianorthodox.org

፩ኛ. ፊደልና አቡጊዳ

፪ኛ. ቁጥር (አኅዝ)

፫ኛ. ንባብና ጽሕፈት

፬ኛ. ሥነ ፍጥረትና ሕገ እግዚአብሔር

፭ኛ. አምስቱ አዕማደ ምሥጢር

፮ኛ. ጸዋትወ ዜማ

፯ኛ. የግዕዝ ቋንቋና ቅኔ

፰ኛ. የመጻሕፍት ትርጓሜ

፱ኛ. አቡሻህር (የቁጥር ትምህርት)

፲ኛ. ሥዕል ሐረግና ቅርጻ ቅርጽ (አርት)

## ፩ኛ. ሀ ፊደል

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና እምነት የፊደል ስልት ተጀመረ የሚባለው በሄኖስ ዘመን ነው። ሄኖስ እግዚአብሔርን በማገልገል የታወቀ ደግ ስለ ነበር ለደግነቱ መታወቂያ ይሆነው ዘንድ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሕግ መጣሪያ የሚሆነው ፊደል በጸፍጸፈ ሰማይ ተገልጦ ታይቶታል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፊደልን ለሥነ ጽሕፈት በር መክፈቻ በማድረግ ተጠቅሞበታል። ስሙንም ጽሑፍ ለማለት ፊደል ብሎታል።

የግእዝ ፊደላት ቁጥራቸው ፳፮ ነው። የግእዝ ፊደላችን ጥንታውያን መጽሐፍቶቻችን ሁሉ የተጻፉበት ብዙ ድርሰቶች የተደረሱበት ነው። የግእዝ ፊደል እስከ ሳብዕ አልነበረውም በግእዙ ብቻ ይነገርና ይጻፍ ነበር።

ለምሳሌ ብርሃኑ ለማለት በረሀነ፣ ጥበቡ ለማለት ጠበበ ይል ነበር ማለት ነው። ይህ አነጋገርና አጻጻፍ እምነተ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እስከ ገባ ድረስ ያገለግል እንደ ነበር ከታሪክ ማኅደር መረዳት ይቻላል። ከዚህ የተነሣ በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን አመራር ሰጭነት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የግእዝን ፊደል በሁለት ወገን በመከፈል ሕዝቡ እንዲገለገልበት ማድረጋቸው ለዘለዓለም የሚያኮራቸውና የሚያስ መሰግናቸው ነው። አንደኛው ክፍል ቀደም ሲል የሕዝቡ መገልገያ የነበ

www.ethiopianorthodox.org

ረው በ «አ» ጀምሮ እስከ «ፐ» አ.በ.ገ.ደ... በመባል ይታወቅ የነበረው የጥንቱ የኢትዮጵያ ፊደል ሲሆን ሁለተኛው ፊደል ደግሞ ለአጠቃቀም በሚያመች ሁኔታ በሊቃውንት ተሻሽሎ እስከ ዛሬ እየተሠራበት ያለውና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቀምበት ከሀ–ፐ ያለው ፊደል ነው።

እነዚህ ፊደላት እንደ ዕብራይስጡ ፊደል በእግራቸው በወገባቸውና በራሳቸው ልዩ ልዩ ቅጥያዎችና ምልክቶች በማድረግ ካዕብ፣ ሣልስ፣ ራብዕ፣ ሐምስ፣ ሳድስ፣ ሳብዕ በሚል የድምጽ መስጫና ንቁጦች (አናጋሪ) ዋየል እንዲነበቡ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው። የግእዝ ፊደል ግዕዝ የተባለበት ምክንያት ቀደም ሲል እንደ ተናገርነው በአንደኛው ፊደል ብቻ ይነገር ስለነበር ነው።

እስከ ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእነዚህ የግዕዝ ፊደላት ብቻ ሲሠራ ኖሮአል እየዋለ እያደረ የአማርኛ ቋንቋ ሲስፋፋ የአማርኛ ፊደላት ሊፈጠሩና ከግዕዙ ፊደላት ጋር አብረው የአማርኛው ጽሑፍ ሊጻፍባቸው ቻለ። የአማርኛ ፊደላት የተባሉበትም ምክንያት በግዕዝ መጻሕፍት የማይገኙና በጥንታዊ አነጋገርም የማይገቡ ስለ ነበርና በኋላ ዘመን የገቡ ስለሆነ ነው ቁጥራቸው ፯ ነው።

በተጨማሪ የግዕዝና የአማርኛ ፊደላት ዲቃሎች የሚባሉ ሌሎች ፊደላት አሉ። እነዚህም የግዕዝ ፊደላት ዲቃሎች የሚባሉት ቁጥራቸው ፬ ሲሆን የአማርኛ ፊደላት ዲቃሎች የሚባሉት ደግሞ ቁጥራቸው ፲፰ ነው።

## ለ. አቡጊዳ

አቡጊዳ እንደ አሁኑ ፊደል የቁጥር ትምህርት አለው ማለትም የፊደሎች ቅርጽ በተለያየ ቦታ ሲገኝ ተማሪው እንዴት ሊለያቸው እንደሚችል ሆኖ የተዘጋጀ ስለሆነ ፊደሎቹን አንድ በአንድ እየቆጠረ ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይ፣ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራም ወደ ቀኝ እያለ እየመላለሰ ይማራል።

## ፩ኛ. ቁጥር (አኃዝ)

ብኢትዮጵያ የቁጥር ስልት አጠቃቀም በቅርብ ጊዜ የተጀመረ ሳይሆን ኢትዮጵያ ፊደልንና ጽሑፍን ማስተማር ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ ሲሠራበት የኖረ ነው። የሌሎች ዓለማት ሕዝቦች አብዛኞዎቹ


www.ethiopianorthodox.org

የዓረብኛ የቁጥር ስልት ሲጠቀሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የራሱ በሆነ ፊደል ብቻ ሳይሆን የራሱ በሆነ አኀዝም (ቁጥር) ሲጠቀም የኖረና አሁንም የሚሠራበት ነው። ሕጻናትም ይህንን የአኀዝ (ቁጥር) ትምህርት ከፊደሉ ጋር አብረው ይማሩታል።

## ፫ኛ. ንባብና ጽሕፈት

### ሀ. የንባብ ትምህርት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የንባብን ትምህርት ለማስተማር የምትጠቀምባቸው መጻሕፍት:-

፩ኛ. ፊደል ሐዋርያ (፩ኛ መልእክተ ዮሐንስ)

፪ኛ. ገበታ ሐዋርያ (መልእክታተ ሐዋርያት) አርጋኖን፣ ውዳሴ አምላክ

፫ኛ. ወንጌለ ዮሐንስ

፬ኛ. መጻሕፍተ ሰሎሞን

፭ኛ. መጽሐፈ ሲራክ

፮ኛ. መዝሙረ ዳዊት ናቸው።

ፊደለ ሐዋርያና ገበታ ሐዋርያ የተባሉት የትምህርት ዓይነቶች ከአቡጊዳ ቀጥለው የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ናቸው ተማሪው እነርሱን የዘር መለያ፣ የንባብ መማሪያ አድርጎ ከፊደል ቈጠራ እንደ ወጣ የሚጠቀምባቸው የመማሪያ ዘዴዎች ናቸው። ፊደለ ሐዋርያና ገበታ ሐዋርያ የተባሉት ራሳቸውን የቻሉ መጻሕፍት ስለ ሆኑ መልካቸውን ቅርጻቸውን በመለየት ተማሪው ጠንቅቆ ይቈጥራል፣ ያግዛል፣ ውርድ ንባብም ያነበባል ተማሪው በደንብ የፊደላትን ዘር መለየቱ ሲረጋገጥ ደግሞ ቁም ንባብ ያነበባል «ቅድመ መሐርዎሙ ለውሉ ድከሙ መጽሐፈ ሰሎሞን ወሲራክ ወመዝሙረ ዳዊት ለልጆቻችሁ አስቀድማችሁ የሰሎሞንና ሲራክን እንዲሁም የዳዊት መዝሙርን አስትምሩአቸው» ሲል ዮሐንስ አፈወርቅ የተናገረውን መሠረት በማድረግም በተከታታይ እነዚህን መጻሕፍት እንዲያነብ ይደረጋል።

### ለ. የጽሕፈት ትምህርት

ጽሕፈት ለኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ ሙያ ትልቅ ቁም ነገር ነው። ተማሪውም የፊደል ቆጠራ ትምህርት እንደ ጀመረ ከፊደሉ ቁጥር ጋር ጽሕፈቱንም አብሮ ያጠናል።


www.ethiopianorthodox.org

የዘመኑን ትውልድ ወደ አድናቆት የመለሱትን ታላላቅ የብራና መጻሕፍት በቁም ጽሕፈት እየጻፉ ያቆዩን በዚህ መልክ የተማሩ ሁሉ ናቸው። ብዙዎች መምህራን ከትምህርቱ አንዱ የቁም ጽሕፈት ስለ ሆነ ደረጃ ሰጥተው የፊደሎችን ቅርጽ በመጠበቅ የቁም ጽሕፈት ትምህርትን ለተማሪዎቻቸው ያስተምራሉ።

የአጻጻፉ ሥርዓትም ቀጥሎ እንደ ተገለጠው ነው።

፩. አርእስት – አርእስት የሚባለው የመጽሐፉ ራስ ያልተጻፈበት ቦታ ነው።

፪. ኅዳግ የሚባለውም በግርጌ ያለው ማለትም ያልተጻፈበት ባዶ ቦታ ሲሆን ትርጉሙም ያልተጻፈበት ወይም የተተወ ማለት ነው።

፫. ግሌት – ግሌት የሚባለው ወደ መጨረሻው ያለው ያልተጻፈበት ቦታ ነው።

፬. ኅላፍ – ኅላፍ ሁለተኛ ቅጠል የሌለው ዕኩሌታ ቅጽ ነው።

፭. ሐውልት – ሐውልት የሚባለው በሁለቱ ዐምዶች መካከል የማይጻፍበት ቦታ ነው።

፮. ዓምድ – ዓምድ የሚባለው በሐውልት ተከፍሎ ጽሑፉ ያረፈበት ነው።

፯. ሲራክ – ሲራክ ወሰፌው ያለፈበት ሰምበሩ ወይም መስመሩ ነው።

፰. ምስማክ – ምስማክ ዕጥፋቱን እንደ ወንዝ አማክሎ ወደ ጥራ ያለው ማዶና ማዶው ነው።

፱. ማኅጸን – ማኅጸን በፊደል መካከል የሚገኘው ቦታ ነው።

፲. ሕጽን – ሕጽን በፊደሉ ውስጥ የሚገኘው ክፍት ቦታ ነው።

፲፩. መስመር – መስመር ቀለም የሚወድቅበት ተላላው ነው።

፲፪. ቀለም – (ኅርወት) ቅርጽ ማለት ነው።

፲፫. ልክ ንባብ – ልክ ንባብ ቃል ማለት ነው። ይህንንም የመሰለ ሌሎች ይገኛሉ።

እንዲሁም ጽሕፈቱ ሲጻፍ ሥርዓተ ፊደልን በመጠበቅ ነው። ለምሳሌ – ሀሌታው ሀ.፤ ሐመሩ ሐ፤ ብዙኃኑ ኀ፤ ንጉሡ ሠ፤ እሳቱ

www.ethiopianorthodox.org

ሰ፣ አልፋው አ፣ ዓይኑ ዐ ጸሎቱ ጸ፣ ፀሐዩ ፀ፣ እንዲሁም ሌሎቹ ሆኄያት ሳይደባለቁ ተጠብቀው በየአገባባቸው ይጻፋሉ።

በተለይም ከፊደሎቹ ውስጥ ግዕዙና ራብዑ ቅርጻቸው ልዩ ይሁን እንጂ በድምጽ ስለሚመሳሰሉ ለማያውቃቸው ለይቶ ለመጻፍ ያስቸግራሉ።

ለምሳሌ ሀ. ግዕዝና ሃ ራብዕ፣ ሐ ግዕዝና ሓ ራብዕ፣ ኀ ግዕዝና ኃ ራብዕ፣ እንዲሁም አ ግዕዝና ኣ ራብዕ፣ ዐ ግዕዝና ዓ ራብዕ እነዚህ በጥንቃቄ ካልተጻፉ ትርጉሙንና ምሥጢሩን ስለሚያፋልሱ መምህራኑ በከፍተኛ ጥንቃቄ ባሕርያቸውን ጠብቀው ያስተምሩዋቸዋል።

## ፬. ዜማ

የቃሉ ትርጓሜ ዜማ ማለት ስልት ያለው ጩኸት ወይም ድምጽ ማለት ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ዜማ ማለት ለጆሮ የሚያስደስት ለስሜትም ትርጉም የሚሰጥ ድምጽ ነው። ዜማ ማለት በልዩ ሕብር የተደራጀ ወይም የተቀነባበረ ድምጽ ማለት ነው። ማንኛውም ድምጽ በከፍተኛና በዝቅተኛ የድምፅ መያያዝ መካከል ቃና አለው። ቃናው ግልጽና ለመለየት ቀላል ከሆነ ድምፁ እንደ ዜማው በዜማ ምልክት ወይም በኖታ ሊገለጽ ይችላል።

ስለዚህ ዜማ ሲባል በአጠቃላይ የምሥጋና መዝሙር የደስታ ድምጽ ማለትም ነው።

ዜማ ከመላእክት ጋር አብሮ የተገኘ ቀዳማዊ ነው። ይህንንም በማስመልከት ራሱ ቅዱስ ያሬድ «ቀዳሚ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ ዘ መላእክት ግናይ» በማለት ቀዳማዊነቱን አርያም በተባለው ድርሰቱ ገልጦ አስረድቶአል።

ዜማ ቀደማዊ ብቻ ሳይሆን ታላቅም ነው። ይህንንም ቅዱስ ያሬድ ሲያስረዳ ዓቢይ ዜማ ተሰምዐ በሰማይ ዘመላእክት ግናይ እንዘ የዓርግ ወልድ ዲበ መንበሩ ኵሎሙ መላእክት ትንሣኤሁ – ዘመሩ» ሲል ገልጾታል።

ዜማ በኢትዮጵያችን በተለይም በመንፈሳዊ ክፍል ማለትም በቤተ ክርስቲያን ጽኑ መሠረት ይዞ ትውልድ የሚከተለው መደበኛ ትምህርት ለመሆን የበቃው በአምስተኛውና በስድስተኛው መቶ ዓመት መካከል

www.ethiopianorthodox.org

በ፳፻፬ ዓ.ም በአጼ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ሲሆን ደራሲውም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ነው።

ዜማ ሰውም ሆነ እንሰሳ ያለ አስተማሪ በሕገ ተፈጥሮ የሚያገኘው የስሜት መግለጫ ሲሆን በተለይ ሰው ግን ዜማን ከዕለት ወደ ዕለት እያሻሻለ ከልዩ ልዩ መሣሪያዎች ጋር እያስማማ ለኀዘንም ሆነ ለደስታ ስሜቱን ይገልጽበታል። ዜማ ከተፈጥሮ ጋር የተያያዘና የተሰናሰለ በመሆኑ ዜማ የሌለው ሕዝብ በዓለም ላይ አይኖርም። ዜማ ቤተ ክርስቲያንን ከማገልገሉም በላይ ለመዝሙር፣ ለደስታና ለኀዘን፣ ለቀረርቶ፣ ለዘፈን ለእንጉርጉሮ፣ በአጠቃላይ እነዚህን ለመሳሰሉትና ዓለም ለሚፈልጋቸው የስሜት መግለጫዎች ሁሉ ጠቃሚ ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ዜማን መንፈሳዊና ዓለማዊ ብሎ ከሁለት መክፈል ይቻላል። እነዚህ ሁለት ክፍሎች የስም ልዩነት ያላቸውን ያህል በአገልግሎትና በአፈጻጸም በኩልም ልዩነት አላቸው። ይኸውም እንደሚታወቀው መንፈሳዊ ዜማ የሚባለው ካህናት በቤተ ክርስቲያን፣ አንዳንድ ጊዜም ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በተለያዩ ዕለታትና በዓላት በመዓልትም ሆነ በሌሊት በሠርክም ሆነ በነግሕ ሥርዓትና መልክ በአለው ሁኔታ እየተሰበሰቡ እግዚአብሔርን በማመስገን የሚያዘሙት ወይም የሚዘምሩት ዜማ ነው። በመሆኑም በምስጋና ቃል እግዚአ ብሔርን እንደሚያመሰግኑት መላእክት እንሁን በየማዕርጋቸውና በየማኅ በራቸው በየነገዳቸውና በየሠራዊታቸው በየስማቸው በየቁጥራቸውም የሚጋርዱ አሉ። የሚከቡም አሉ። በዜማ የሚያመሰግኑም አሉ የሚዘምሩም አሉ» በማለት ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የተናገረውን መጥቀሱ ይበቃል መጽሐፈ ቅዳሴ (አት.ቁጥር ፶፫)፣

ይህ አገላለጽ የሚያመለክተን ዜማ በምድራውያን ፍጡራን ብቻ ሳይሆን በሰማውያን መላእክትም ዘንድ እንኳ ሳይቀር ምን ያህል ክብርና ተወዳጅነት ያለው መሆኑን ነው።

ዓለማዊ ወይም ሕዝባዊ ዜማ የሚባለው ደግሞ ሕዝቡ እንደእየቋን ቋውና እንደ እየባህሉ በኅብረትም ሆነ በተናጠል ቡድን እየአቋቋመ በተለያዩ ዕለታትና በዓላት ለምሳሌ በሠርግ ቤት፣ በአዉዳ፣ በውቂያና በመሳሰሉት ሁሉ የሚያዜመው ዜማ ወይም ዘፈን ነው። በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊ ለዜማ አገልግሎት የሚውሉት መሣሪያዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

፩ኛ. ከበሮ፤
፪ኛ. ጸናጽል፤
፫ኛ. መቋሚያ፤
፬ኛ. መሰንቆ፤
፭ኛ. እምቢልታ፤
፮ኛ. መለከት፤
፯ኛ. ክራር፤
፰ኛ. በገና፤
፱ኛ. ዋሽንት፤
፲ኛ. እንዚራ፤
፲፩ኛ. አርጋኖን በመባል ይታወቃሉ።

በአጭሩ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዐበይት መሣሪያዎች ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ኅብረተ ሰብእ የፈጠራ ውጤቶች ስለ ሆኑ ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ኅብረተ ሰቡን የሚያኰሩ ናቸው።

## ሀ. የዜማ ምልክቶች

ኢትዮጵያ ሀገራችን የቤተ ክርስቲያን ዜማዎችን በምልክት (ኖታ) እንዲዜሙ ያደረገች ጥንታዊትና ታሪካዊት ሀገር መሆኑዋን የዓለም ሊቃውንት ይመሰክራሉ። ሥራውም ራሱ ምስክር ነው።

በመሠረቱ ምልክት ሲባል የአንድ ነገር ማረጋገጫ፤ ማስረጃ፤ ማወቂያና ማሳወቂያ መገንዘቢያም ማለት ነው።

በዚህ መሠረት ምልክት የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን በሌላም በተለያዩ ነገሮች ሊያገለግል ይችላል። ማለትም በዜማ በትርጓሜ በንባብና በመሳሰሉት ሁሉ ማለት ነው። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሕፈት ስልት መሠረት የዜማ ምልክት፤ የትርጓሜ ምልክት፤ የንባብ ምልክት፤ አሁን በዘመናችንም የአቋቋምና የወረብ ምልክት እየተባለ ይጠራል።

በመሆኑም ዜማውን በምልክት ምልክቱን በዜማው በመወሰን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበት ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበት ለደስታም ለኀዘንም መግለጫ የሆነ ራሱን የቻለ ምልክት ያለው ትክክለኛ መንገድን የተከተለ መሆኑን የምንረዳበትና የምናስረዳበት የጥበብ ጥበብ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## የዜማ ዓይነቶች

በቤተ ክርስቲያናችን የዜማ ዓይነቶች ሦስት ናቸው። እነሱም ግእዝ፣ ዕዝል፣ አራራይ ይባላሉ። ምሳሌያቸውም ግዕዝ በአብ፣ ዕዝል በወልድ፣ ዓራራይ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል።

ግዕዝ – ማለት ጽኑዕ ማለት ነው። በአብ የተመሰለበት ጽኑዐ ባሕርይ ለማለት፣

ዕዝል – ማለት ብርቱ ማለት ነው በወልድ የተመሰለበት መከራ ለመቀበል የበረታ ለማለት ነው።

አራራይ – ማለት አራኅራኂ ወይም የሚያራራ ማለት ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተመሰለበት መንፈስ ቅዱስን የሰውን ልቡና የሚያራራ ለማለት ነው።

## ጸዋትወ ዜማ

ጸዋትወ ዜማ (የዜማ ወገኖች) አምስት ናቸው።

እነርሱም:-

፩ኛ. ድጓ ጾመ ድጓ፤

፪ኛ. ምዕራፍ፤

፫ኛ. ዝማሬ፤

፬ኛ. መዋሥዕት፤

፭ኛ. ቅዳሴ ናቸው።

## ፩ኛ ድጓ

ድጓ የሚለው ቃል የዜማ መጽሐፍ ስም ነው። እሱም ቅዱስ ያሬድ በ፭፻፵ ዓ.ም የደረሰውና ያዜመው (የዘመረው) ነው። በመሠረቱ ድጓ ማለት መዝሙረ ስብሐት፣ መዝሙረ ኀዘን ማለት ነው። ድጓ ዮሐንስ፣ አስተምህሮ፣ ፋሲካ ተብሎ በሦስት ይከፈላል።

## ጾመ ድጓ

ጾመ ድጓ ከድጓው አንድ ክፍል የሆነ ለጾም ወራት አገልግሎት የተቀመረ ነው። መጀመሪያ በድጓው ክፍል በአስተምህሮ ይገኝ ነበር። ነገር ግን በ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በደብረ ንጉድጓድና በደብረ እግዚአብሔር የነበሩ ሊቃውንት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን መሪ በማድረግ


www.ethiopianorthodox.org

ከአስተምህሮው ድጓ አውጥተው ራሱን የቻለ ክፍል እንደ አደረጉት ይነገራል።

ጾመ ድጓ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በዓቢይ ጾም ወራት

ሀ. በሰዓት

ለ. በዕለት

ሐ. በሳምንት የሚጸለይና የሚዘመር ሁና የተዘጋጀ ነው።

## ፪ኛ. ምዕራፍ

የምዕራፍ ዜማ ትምህርት የዘወትርና የጾም ምዕራፍ ተብሎ በሁለት ክፍል ይከፈላል።

### ሀ. የዘወትር ምዕራፍ

የዘወትር ምዕራፍ የሚባለው ዓመቱን ሳይጠብቅ በዓመቱ ውስጥ ባሉት ሳምንታትና በዓላት ወቅቱን እየጠበቀ በአገልግሎት ላይ የሚውል ነው።

### ለ. የጾም ምዕራፍ

የጾም ምዕራፍ የሚባለው ደግሞ በጾመ አርብዐና በአንዳንድ የምሕላ ቀኖች የሚዘመር ነው። የሁለቱም ክፍሎች ዋና መሠረታቸው የዳዊት መዝሙርና ድጓ ወይም ጾመ ድጓ ነው። የትምህርት አሰጣጣቸው እንደ ድጓው ወይም እንደ ዝማሬውና እንደ መዋሥዕቱ በመጽሐፍ ሳይሆን፣ በቃል የሚጠኑ ናቸው።

## ፫. ዝማሬ

ዝማሬ ማለት መዝሙር፣ አዘማመር፣ ዝመራ በዜማ የሚቀርብ ማኅበራዊ ምሥጋናና ጸሎት ነው። ይህም ከአምስቱ ጽዋትወ ዜማ አንዱ የሆነ በቅዳሴ ጊዜ የሚቃኝ የሚዜም የሚዘመር የጸሎተ ቅዳሴውን ምሥጢርና ዓላማ ተከትሎ የሚሔድ ነው። ይኸው ጸሎተ ቅዳሴው ግእዝ ሲሆን በግእዝ ዕዝል ሲሆን በዕዝል የሚዘመር ነው።

## ፬. መዋሥዕት

መዋሥዕት ለዕለተ ሙት ፍትሐትና ለሙት ዓመታት ለመላሰሉትም ሁሉ የሚጸለይ ጸሎት ነው። ከዚህ በስተቀር መዋሥዕት በበዓለ ሰንበት በጌታችን በእመቤታችን፣ በጻድቃንና በሰማዕታት በመሳሰሉት በዓላት ሁሉ በዜማ ይጸለያል።

www.ethiopianorthodox.org

መዋሥዕት ከዝማሬው ጋር የተደረሰ የታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ነው። በትምህርትም ጊዜ ከዝማሬው በአለመለየት መምህራኑ ለተማሪዎች አብረው ያስትምሩታል የማስመስከሪያው ቦታም በደቡብ ጐንደር ሀገረ ስብከት በጋይንት አውራጃ ልዩ ስሙ ዙር አባ በተባለው ገዳም ነው።

## ፫ኛ. ቅዳሴ

የቅዳሴ መጻሕፍት በየጊዜው የተደረሱና ደራሲያኑ ልዩ ልዩ ሊቃውንት ሲሆኑ ዜማውን ያቀናበረው አንድም የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ነው።

ስለ ቅዳሴ ትምህርት ከቅዱስ ያሬድ ጀምሮ በጥንት ዘመን ከዝማሬ መዋስዕት ጋር በዙር አባ ያስተምሩት ያስመሰክሩትም እንደ ነበር ይተረካል። እየቆየ ግን የቅዳሴ ምስክር ቦታ ተብሎ ይነገርለት የነበረው በታሪክም ጎልቶ እስከ አሁን ድረስ የሚታወቀው ስለልኩላ የሚባለው ገዳም ነው።

በቅርቡ በአጼ ምኒልክ ዘመን መንግሥት ግን በተጨማሪ ደብረ ዓባይ የቅዳሴ ምስክር ቦታ ሆኖአል በመጀመሪያ ደብረ ዓባይን የቅዳሴ ምስክር ቦታ ያስደረጉት መምህር ገብረ ኢየሱስ የተባሉ መምህር ናቸው እሳቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ስለልኩላ ተምረው ያስመረቁም በዚያው ነበር፣ ነገር ግን በጣም ድምጻዊ ስለ ነበሩ እራሳቸው ወዝ እየሰጡ ዜማውን እያስረዘሙ በማዜማቸው ዜማቸው ተወዳጅ ሆነ ወደ ደብረ ዓባይም ገብተው ወምበር ዘረጉ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መምህር ገብረ ኢየሱስ የቅዳሴ ምስክር ደብረ ዓባይም የምስክር ቦታ ለመሆን በቁ፣

የቅዳሴ ዜማ ወዙ (ለዛው) እንደ ዝማሬና መዋስዕት ለየት ያለና ረዘም ያለ ቢሆንም ምልክቱ እንደ ድጓው ነው።

ቅዱስ ያሬድ በዜማ የደረሳቸው የኢትዮጵያ ቅዳሴዎች 14 ናቸው። እነዚህም:-

፩ኛ. ቅዳሴ ሐዋርያት

፪ኛ. ቅዳሴ እግዚእ

፫ኛ. ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ

፬ኛ. ቅዳሴ ሕርያቆስ (ቅዳሴ ማርያም)

፭ኛ. ቅዳሴ ሠለስቱ ምዕት

፮ኛ. ቅዳሴ አትናቴዎስ

፯ኛ. ቅዳሴ ባስልዮስ

www.ethiopianorthodox.org

፰ኛ. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ እኅወ ባስልዮስ

፱ኛ. ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ

፲ኛ. ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ

፲፩ኛ. ቅዳሴ ቄርሎስ

፲፪ኛ. ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ

፲፫ኛ. ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ

፲፬ኛ. ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ዘአርማንያ ናቸው።

ከነዚህም ፍሬ ቅዳሴያት ሌላ ከፍሬ ቅዳሴ በፊት የሚጸለዩ:-

፩ኛ. ሥርዓተ ቅዳሴ

፪ኛ. ኪዳን

፫ኛ. ሊጦን

፬ኛ. መስተብቍዕ

፭ኛ. ዘይነግሥ

የተባሉ በዜማ የሚጸለዩ ድርሰቶች ሁሉ ዜማቸው የተደረሰው በቅዱስ ያሬድ ነው። እንዲሁም ቅዱስ ያሬድ በትምህርት የወለዳቸው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተባሉት ታላቅ ሊቅ በንባብና በዜማ የደረሱት በሌሊትና በመዓልት የሚጸለይ ሰዓታት የተባለ ድርሰት አለ የዚህም ድርሰት የዜማው ላህይ ለየት ያለ ቢሆንም ምልክቱ እንደ ድጓና እንደ ቅዳሴ ነው።

## የቅዱስ ያሬድ የዜማ ዘር (ድርሰት) ምንጮች

ሀ. ብሉይ ኪዳን፣

ለ. ሐዲስ ኪዳን፣

ሐ. መጻሕፍተ ሊቃውንት

መ. መጻሕፍተ መነኰሳት

ሠ. ድርሳናትና ሌሎችም ናቸው።

ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ሊደርስ የቻለው ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መጻሕፍት መሠረት በማድረግ ንባቡን ለዜማው እንደሚስማማ በማቃናትና መሠረተ አሳቡን ሳይለቅ ንባቡ ከነምሥጢሩ በመንፈስ

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ተገልጾለት እንጂ እንዲሁ በዘፈቀደ ከልቡ አንቅቶ፣ ከአፉ አውጥቶ አልተናገረውም።

## አቋቋም

ከቁም ዜማ የተለየ ሆኖ በመቋሚያ በጸናጽልና በከበሮ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት የማሕሌት ዜማ ነው። የቤተ ክርስቲያናችን የማኅሌት ሥነ ሥርዓት ጥንታዊ ሲሆን የተጀመረው በቅዱስ ያሬድ ነው። ጀማሪ ውም እሱ ራሱ ነው፣ እሱ በጸናጽል እና በከበሮ ምሥጋና ለእግዚአብሔር ያቀርብና ማኅሌትም ይቆም እንደ ነበር በታሪክም በሥዕልም ሁል ጊዜ ይገለጻል።

# የግዕዝ ቋንቋና ቅኔ

## ሀ. የግዕዝ ቋንቋ

ከባቢሎን ግንብ መፍረስ በኋላ አንድ የነበረ ፊደልና ቋንቋ ሲለያይ የሰዎች ቋንቋ በየነገዳቸውና በየስማቸው ተሰይሞዋል። በሀገራችንም ከግዕዝ ቋንቋ በፊት የሳባንና ሳባን የመሳሰሉ ቋንቋዎች እንደ ነበሩ ይታወቃል። ይኸውም በየዋሻውና በየድንጋዩ በየሐውልቱም ላይ ተጽፎ ይገኛል። የግዕዝ ቋንቋ ግን በአብርሃም የልጅ ልጅ በያዕቆብ ዘመን በባብዕል–መንደብ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የሴማውያን (ነገደ ዮቅጣን) ቋንቋ ነው።

ግዕዝ ማለት አንድ ጥንት መጀመሪያ ማለት ነው መጀመሪያነቱም ከካዕብ እስከ ሳብዕ ላሉት ዋየሎች ሲሆን በቋንቋ መጀመሪያነቱ ደግሞ በባቢሎን መበታተን ምክንያት ከተፈጠሩት በብዙ ክፍለ ዓለማት የሚገኘው የሰው ልጅ ከሚጠቀምባቸው ልዩ ልዩ ሴማዊ ቋንቋዎች የተለየ የመጀመሪያው ሰው አዳም ይናገርበት የነበረ ጥንታዊ ቋንቋ በመሆኑ ነው። ሴማውያን ከነገደ ካም ከኩሽ ልጆች እየተጋቡና እየተዋለዱ የኩሽን መንግሥት ወርሰው እነሱ አግአዝያን ተብለው ሀገሪቱንም ብሔረ እግዓዚት አሰኝተው ሲኖሩ ግዕዝ ቋንቋቸው እያበበ እስከ ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ሕዝባዊ ወይም ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ ቆይቷል።

በዚህ ዘመን የአማርኛ ቋንቋ ብቅ ብሎአል፣ ቢሆንም አማርኛ እስከ አሁን ድረስ የሚነጋገሩበት ወይም የዘር መነጋገሪያ ቋንቋ እንጂ በቤተ መንግሥትና በቤተ ክርስቲያን የሥራ ቋንቋ አልነበረም።

www.ethiopianorthodox.org

ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን የሚጸለይበት፣ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት፣ በአጠቃላይ ሥርዓተ አምልኮት የሚፈጸምበት፣ ሁለተኛም በቤተ መንግሥት የሰው ጉዳይ የሚታየበት፣ የሚተችበት፣ የሚፈረድበት፣ የነገሥታቱ ታሪክ የሚመዘገብበት አልነበረም።

ስለዚህ ነው በቤተ ክርስቲያናችን ተጠብቀው ያሉት በውጭ ሀገርም ሳይቀር የሚገኙት የሃይማኖት የሥርዓተ አምልኮት፣ የትምህርትና የታሪክ መጻሕፍታችን በግዕዝ ቋንቋ ተጽፈው የሚገኙት።

አሁን ግዕዝ የቤተ ክርስቲያን የግል ሀብት መስሎ በቤተ ክርስቲያን ብቻ «ይቤ መተርጕም» እየተባለ መጻሕፍተ ብሉያትና መጻሕፍተ ሐዲሳት እንዲሁም መጻሕፍተ ሊቃውንት እየተተረጐሙበት እግዚአብሔር አምላክ እየተመሰገነበት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛል።

የግዕዝ ቋንቋ በሀገራችን በኢትዮጵያ ጥንታዊ መሆኑ ይታወቃል። በየአደባባዩና በቤተ መንግሥት ሰዎችንና አሳባቸውን በግልጽ በማስተዋወቅ ሥጋዊና መንፈሳዊ ታሪካቸውን በመመዝገብ የሰጠውን የረዥም ዘመን አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን ትመሰክርለታለች። ታስታውሰው ማለች። የአገር ውስጥ፣ የውጭ አገር ሊቃውንትም ያረጋግጡለታል።

በመሠረቱ ግዕዝ የተለያዩ ባሕርያት ያሉት በአንድ ቃል ብቻ ብዙ መልእክታት ማስተላለፍ የሚቻልበት ኀብር የሆነ ሰፊ ቋንቋ መሆኑ ግልጽ ነው።

የኢትዮጵያን ታሪክ አጠናለሁ እመረምራለሁ የሚል ማንም ተመራማሪ የአባቶቹን ታሪክ ማጥናትና መመራመር የሚችለው በቅድሚያ የግዕዝን ቋንቋና አገባቡን አጣርቶና አጥንቶ ሲገኝ ነው። በተጨማሪም በግዕዝ ቋንቋችን ውስጥ ለባህላችንና ለታሪካችን እድገት ለአሁኑ የግምባታ ሒደታችንና ለእውቀታችን መለኪያ የሚሆኑ ብዙ ቃላት አሉ። ቃላቱን እየመረመሩ በየሚጠቀሙበት ሐረግ እያስገቡ መጠቀም የቃላትን ብድር ፍለጋ ወደ ውጭ ከመሰደድ ያድናል ራስን በራስ ያስተምራል፣ ያኮራል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዜማን ካስተማረች በኋላ ይህን የግእዝ ቋንቋ ትምህርት ከነቅኔው ታስተምራለች። የግዕዝ


www.ethiopianorthodox.org

ትምህርት መጀመሪያው ግሥ ይባላል ተማሪው ቅኔን ከመቁጠሩ በፊት ግሥ መግሠሥንና ማውረድን ያጠናል።

## ለ. ቅኔ

ቅኔ ማለት መገዛት አገልግሎት ነው። ለምሳሌ ቅኔ ደብተራ ቅኔ ማኅሌት እንዲሉ ከዚህም ጋር በቅኔ ሙሾ ግጥም ቅንቀና የፍትሐት የልቅሶ ዜማ እንዲሁም የምስጋና ግጥም መግጠም ይቻላል።

የጥንት ሰዎች በተለይ ዕብራውያን በቅኔ ግጥም እየገጠሙ፣ ማለት ቅኔ እየተቀኙ አምላካቸውን ያመሰግኑ ነበር። በተለይም ነቢዩ ዳዊት ራሱ ግጥም እየገጠመ ፈጣሪውን ከማመስገኑ በላይ ሌላውም ሰው በቅኔ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ሲያዝዝ «ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሐት» በማለት ዘምሯል፣ ሌላውንም አዝዟል። በኋላም ኢትዮጵያዊው ሊቅ የዜማና የቅኔ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሐት ሲል ዘምሯል።

የቅኔው ደራሲ ቅዱስ ያሬድ እንደ ሆነ ቢታወቅም ከአሥራ አራተኛው ምእት ዓመት ጀምሮ በየጊዜው የተነሡት እነ ሐዊራ፣ መንክራ፣ እስክንድራ፣ እስካንድራ አቢዳራ ደቀ እስጢፋተዋነይ ዮሐንስ ገብላዊ የመሳሰሉት ሊቃውንት ሰምና ወርቅን፣ ኅብርን ውስጠ ወይራን አንጻርን ምጸትን ልዩ ልዩ አይነት ጕዳናን የመሳሰሉ ምሥጢራውያን ምሳሌዎችና የምሥጢር ጥልቀትንና ምጥቀትን በመፈልሰፍ አስፋፍተውታል።

ቅኔ በግጥሙ በምሥጢሩ በቃል አሰካኩ ተወዳጅነት ስላለው ብዙ ኢትዮጵያውያን ይማሩታል። ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ሳይቀሩ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድረስ ይማሩት እንደ ነበር ይታወቃል።

## ኪነ ጥበባት በኢትዮጵያ

ኪነ ጥበባት በኢትዮጵያ በምንልበት ጊዜ የቅርጻ ቅርጽን የሥዕላ ሥዕልንና የመሳሰሉትን የፈጠራ ውጤቶች ያጠቃልላል።

የኢትዮጵያ ሊቃውንት የቅርጻ ቅርጽም ሆነ የአሳሳል ስልት እጅግ የተወደደና ከዘመን ወደ ዘመን እየተሻሻለ የመጣ ጥበብ ስለ ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዕድገትና የሀገሪቱን ጥንታዊነት ከሚገልጡት ጥበባት ጥቂቶችን ከዚህ በታች በአጭሩ ለመግለጥ እንሞክራለን።


www.ethiopianorthodox.org

## ሀ. የውቅር አብያተ ክርስቲያናት

ቀደም ባሉት ዓመታት ሊቃውንቱ በዙሪያቸው ከሚገኙት የዓለት ተራራዎችና ኮረብታዎች ፈልፍለው ሕንጻዎችን በማውጣት በኪነ ጥበብ የተራቀቁና የተሳካላቸው የድንጋይ ጠራቢዎችና ጠቢባን ነበሩ የፈጠራቸው ውጤቶች የሆኑት ቅርሶችና ከአንድ ወጥ ድንጋይ ያነጹዋቸው ሐውልቶች የገነቡዋቸው ቤተ መቅደሶችና አብያተ ክርስቲያናት የሚመለከታቸውን የሰውን አእምሮ በአድናቆት ይመስጣሉ።

ከሥራዎቻቸው አብዛኛዎቹ ከ፪ሺ ዓመታት በፊት የተሠሩ መሆናቸው ሲታሰብ ከአድናቆትም በላይ አልፈው ተርፈው የሰውን አእምሮ በአንክሮ ውቅያኖስ ውስጥ ይከታሉ። በኢትዮጵያችን ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ከድንጋይ ፍልፍል የተሠሩ ቤተ መቅደሶችና አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህል በትግራይና በወሎ እንዲሁም በሸዋና በጎንደር በጐጃም የሚገኙትን ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

## ለ. ቅርጻ ቅርጽ

ከላይ የተጠቀሱት የውቅር አብያተ ክርስቲያናት የሥርዓተ አምልኮት መፈጸሚያ በሆኑት ልዩ ልዩ መስቀሎችና ለዓይን በሚማርኩ ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች የተጌጡና በቅርጽ የተዋቡ ናቸው። ይህንንም ለመረዳት የኢትዮጵያ መስቀሎች (ኢትዮጵያን ክሮስስ) የተባለውን መጽሐፍ አንብቦ መረዳትና ማየት ይበጃል። ከዚህም ሌላ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ዕለት ተዕለት አያሌ ቅርጻ ቅርጾች ይገኛሉ።

## ሐ. ሥዕል

ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት በግርግዳቸው በጣራቸው በአምዶቻቸው በየመስኮቶቻቸውና በየበሮቻቸው በጌታ፣ በእመቤታችን፣ በቅዱሳን መላእክት በነቢያት በሐዋርያት በጻድቃንና በሰማዕታት ሥዕሎች የተዋቡና ያሸበረቁ ናቸው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የጌታም ሆነ የእመቤታችን እንዲሁም የቅዱሳን መላእክትም ሆነ የጻድቃንና የሰማዕታትም ሥዕላቸው በየቤተ ክርስቲያኑ መሣሉ ለሰው ልጅ የተደረገውን ድኅነትና ትድግና እንዲሁም ሥራቸውንና

www.ethiopianorthodox.org

ቅድስናቸውን አጉልቶ ለማሳየት በሥዕላቸው ለመማጠንና ምዕመናንን በሥዕል ለማስተማር ነው።

ከዚህም ጋር ሊቃውንቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚጽፉበት ጊዜ በየመጻሕፍታቸው አርእስትና ማዕከል ወደር የማይገኝላቸውን የተለያዩ ሐረጎችንና ሥዕሎችን ይሥላሉ። ይህ የሥዕልና የሐረግ ጥበብ ከሥነ ጽሕፈት ጥበብ ጋር ተዳምሮ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነት የሊቃውንቱን የፈጠራ ችሎታና የኀብረተ ሰቡን በሊቃውንቱ መገልገል አጉልቶ የሚያሳይ የጥበብ ጥበብ መሆኑን መገመት አያዳግትም።

ጥንታውያን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሠዓሊዎች የጌታችንና የእመቤታችንን፣ የጻድቃንና የሰማዕታትን ወዘተ...ሥዕል ሥለው ከማስተማር ጋር የኀብረተ ሰቡን ባሕላዊ አኑዋኑዋር ሥርዓተ አምልኮውን ደስታውንና ኀዘኑን ጀግንነቱንና ድል አድራጊነቱን ሥልጣኔውንና አገር ወዳጅነቱን ጉስቁልናውንና እድገቱን አጉልተው ይሥሉና ለታሪክም ያቆዩት እንደ ነበር ሥራቸው በዓይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ ሕያው ማስረጃ ነው።

ይህም ጥበብ ዘመናትን ያስቆጠረ ከመሆኑም በላይ በዘመናችንም ከአለፈው በተሻለ መልኩ እየተስፋፋና በመሠራትም ላይ የሚገኝ ነው «አባት ያቆየው ለልጅ ይበጀው እንዲሉ የጥንት አባቶቻችን ያቆዩት የዜማና የቅኔ የሥነ ጽሕፈት፣ የቅርጻ ቅርጽና የሥዕል ጥበብ በዘመናችንም በስፋትና በጥልቀት በቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርቱ እየተሰጠ ስለሆነ የዕውቀት ባለቤትና የጥበብ መገኛ የሆነውን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

---

ምንጮች

ሰማንያ አሐዱ ቅዱሳት መጻሕፍት

፩. መዝገበ ቃላት – የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

፪. የኢትዮጵያ ጥንታዊ ትምህርት – የሊቀ ሥልጣናት አባ ሀ/ማርያም

፫. ያሬድና ዜማው – የሊቀ ካህናት ጥዑመ ልሳን ካሣ

፬. የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም – የተክለ ጻድቅ መኩሪያ

፭. የኢትዮጵያ ሥልጣኔ የአቶ በላይ ግደይ

፮. የኢ/ኦር/ተ/ቤ/ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ለኢ/ሕዝብ ዕድገት ያስገኘው አስተዋጽኦ
የሊ/ካ/ብርሃኑ ገ/አማኑኤል (የእጅ ጽሑፍ)

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል አራት

# ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ

«ድንግል ትፀንሳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች» ተብሎ በነቢያት የተነገረለት መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ እነሆ ዛሬ የ፲፱፻፺ ዘመናትን ሲያስቆጥር ሕገ ኦሪትንና ፅላተ ሙሴን ተቀብላ ለአንድ ሽ ዘመናት በአምልኮተ እግዚአብሔር የኖረች ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በንግሥት ሕንደኬ መልዕክተኛ አማካይነት ዜና ልደተ ክርስ ቶስን ሰምታ ማመን ከጀመረች የሁለት ሽ ዓመታትን አስቆጥራለች።

ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥዋ ሥነ ተፈጥሮአዊ ገጽታዋ፣ የአየር ጠባይዋ ሁሉ ሲመዘን ከባሕር ጠለል በታች የ፩፻ ሜትር፣ ከባሕር ጠለል በላይ እስከ ፬ሺ፭፻ ሜትር ከፍታ ያላቸው ታላላቅ ተራሮችን፣ አምባ ምድሮችን፣ ሸለቆዎችን፣ ወንዞችን፣ ሐይቆችን ዓውላላ ሜዳዎችን አጠቃልላ የያዘች ጥንታዊትና ታሪካዊት ሀገር በመሆንዋ በተለይም ከሰሜን የባሕር ጠረፍ እስከ ደቡብ የባሕር ዳርቻ በተዘረጉት ከፍተኛ አምባ ምድሮችዋ፣ ኢትዮጵያውያን ለብዙ ሺህ ዘመናት የኖሩባቸው አካባቢዎች በመሆናቸው በቅድመ ልደተ ክርስቶስ መቅደስ ኦሪት በዘመነ ክርስትና አብያተ ክርስቲያናት የተተከለባቸው ናቸው።

ገና ከጅምሩ ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሁለት ሐዋርያትን መርጦ በኢየሩሳሌም አደባባይ ወንጌለ መንግሥቱን ሲሰብክ ቅዱስ ጴጥሮስን «አንተ ዓለት ነህ በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ» ብሎ መናገሩ ሲመሰክር በአህጉረ አፍሪቃም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ አምልኮተ እግዚአብሔርን ሕገ ኦሪትን ተቀብላ ስትኖር ድኅረ ልደተ ክርስቶስ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ፫፻፴ ዓ.ም ጀምሮ ለዘለዓለም በማይናወፁ ነጭ፣ ብጫ፣ ቀይ፣ አረንጓዴ ሕብረ ቀለም ባላ ቸው የሰሜን ኢትዮጵያ አለቶች ላይ የክርስቶስ ትምህርት፣ ጥምቀት፣ ቤተ ክርስቲያን ቁርባን፣ ስለ ተመሠረተ ጠቅለል ባለ መልኩ

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያን በታሪክ መድረክ የክርስቲያን ደሴት የሚል ስያሜ አሰጥቷታል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ባሕልና ቅርስ በዝርዝር ከመግለጻችን አስቀድሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ የእምነት፣ የባሕልና የቅርስ ዋና ዋና ምንጮችን ጠቀም ጠቀም አድርጎ ማለፉ ለሁሉም ነገር መግቢያ በርና መረማመጃ ጉዳና ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህም የመጀመርያው ጳጳስና ሐዋርያ ወንጌል የሆነው አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ገድል እንዲህ ይላል።

«ወበአሐቲ ዕለት ይቤሉ ፍሬ ምናጦስ ለቅዱስ ሚናስ:-

ኦ አቡየ አነ አነክር ግዕዘከሙ ሰብአ ኢትዮጵያ ግዝረትሰ ወእምነተ ክርስቶስ ሀሎ ኀቤከሙ ጥምቀትሰ ወነሢኣ ቁርባን ኢሀሎ። ወይቤሎ ቅዱስ ሚናስ ዘአክሱም ግዝረተስ አምፅኡ ለነ ሌዋውያን አበዊነ ወእምነተ ክርስቶስ አምጽአለነ ሕጻዋ ለሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ ወበአንተ ጥምቀትሰ ወነሢኣ ቁርባን ኢተፈነወ ሐዋርያ ኀቤነ ሑር ኀበ ሀገረ እስክንድርያ ከመ ታምፅዕ ለነ ጳጳሰ ዘይባርከነ ወዘይቄድሰነ»

«አንድ ቀን ፍሬ ምናጦስ አባ ሚናስን እንዲህ አለው:-

ኢትዮጵያውያን ሥነ ምግባራችሁን አደንቃለሁ ግዝረትና የክርስቶስ እምነት አላችሁ ጥምቀትና ቁርባን ግን የለም ቅዱስ ሚናስም መልሶ ግዝረትን አባቶቻችን ሉዋውያን አምጥተውልናል የክርስትና እምነትንም የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬ ጃንደረባ አምጥቶአል ስለ ጥምቀትና ቁርባን ግን ሐዋርያ ስለ አልተላከልን የለም አሁን ወደ እስክንድርያ ሂድና የሚባርከን ጳጳስ አምጣልን»

በማለት እንደ ተመካከሩና አከታትሎም ቅዱስ ፍሬ ምናጦስ ከቅዱሳን ነገሥት አብርሃ ወአጽብሃ ፈቃድና ትእዛዝ ተቀብሎ ከኢትዮጵያ እስከ እስክንድርያ ድረስ የሚያደርሰው ስንቅ፣ በጉዞው ላይ አረማውያንና አመፀኞች እንዳያስቃዩት ጦር መሣሪያ የታጠቀ (አጃቢ) ሠራዊት አስከትለው በመላክ ፍሬ ምናጦስ ረጅም የበረሃ ጉዞ አቋርጦ ከዘመኑ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ አትናቴዎስ ጋር በመገናኘት ተገቢውን

www.ethiopianorthodox.org

ኦርቶዶክሳዊ መመሪያ በመቀበል መዓርገ ጵጵስና ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ መመለሱን አሁንም ገድለ ሰላማ ሲገለጽ:-

«ወእምዝ አልበሶ ልብሰ ክብር ዘሊቀ ጳጳሳት ወአንበሮ በመንበረ ክብር ወወሀቦ አልባሳተ ክቡራተ ወንዋያተ ቅድሳት ወመጻሕፍተ ብዙኃነ ድርሰናተ ወገድላተ ወኲሳኩሳተ ዘወርቅ ወኵሎ ሠርጓተ ዘቤተክርስቲያን ወመስቀላተ ወጽንሐሐተ ወይቤሎ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ አትናቴዎስ ንሣእ ወሀብኩከ ዘንተ ኵሎ ንዋያተ ቅድሳት አወፌ ለታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ጽዮን ቅድስት አግዓዚት እንተ በሰማያት»

«ከዚህ በኋላ የሊቀ ጵጵስና የክብር ልብስ አልብሶ በከበረ መንበር ላይ አስቀምጠው የከበሩ አልባሳትን፣ ንዋያተ ቅድሳትን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ገድላትንና ድርሳናትን ተግሳጻትንና የቤተ ክርስቲያን ጌጣጌጥን፣ መስቀልንና ጽንሐሕን አዘጋጅቶ ሊቀ ጳጳሳት አትናቴዎስ ይህንን ሁሉ ንዋያተ ቅድስት ሰጥቸሀለሁ ነጻ ለምታደርግና የእግዚአብሔር ታቦተ ሕግ ለሆንችው ታቦተ ጽዮን አበርክት» በማለት አባ ሰላማን በታላቅ ክብር እንደ አሰናበተው በዝርዝር ይገልጻል።

እርሱ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደባት ሀገር ኢየሩሳሌም ጀምሮ በተከታታይ የክርስትና እምነት የተሰበከባቸው ሀገሮች ነገሥታት መሳፍንትና ሕዝብ ስንቅና ሠራዊት አስይዘው የክርስትናን ትምህርት እንዲያመጣላቸው ታማኝ መልእክተኛን መላክ ቀርቶ በእግዚአብሔር ትእዛዝ፣ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በስሜ አጥምቁአቸው» ተብለው የተላኩ ሐዋርያት ተአምራት እየሠሩ በሽተኞችን እየፈወሱ ቢሰብኩአቸው እንኳን የክርስትናን እምነት የተቀበሉት በቀላሉ አይደለም በዚህ ዓለም የማሰቃያ መሣርያ ሁሉ ሐዋርያትን እያሰቃዩ ለብዙ ዘመናት ከቆዩ በኋላ ነው፣ ትምህርተ ወንጌልንና ጥምቀት ክርስትናን ለመቀበል የቻሉት።

ቅዱሳን ነገሥት አብርሃ አጽብሐና የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ስብከተ ወንጌል አምነው ተጠምቀው ሥርዓተ ቁርባ ንን በመፈጸም መቅደሰ ኦሪትን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመለወጥ ከጽላተ ሙሴ ጋር ሌሎች ታቦታትን በመደመር ነገሥቱ እንደ ጳጳሱ ሐዋርያት

www.ethiopianorthodox.org

ሆነው መኳንንቶቻቸውን ሠራዊቶቻቸውንና ሕዝቦቻቸውን አስተ ምረው፣ አሳምነው በማጥመቅ ከ፫፻፴ ዓ.ም እስከ ፫፻፵፱ ዓ.ም ድረስ ለ፲፱ ዓመታት ሙሉ አዲሲቷን ቤተ ክርስቲያን ባለ ፲፪ ቤተ መቅደስ ፳፪ አዕማደ ወርቅ፣ ፴፻፰ መስኮተ ብርሃን፣ ፺፻፺ ቀስተ ደመና ሀረጋዊ ቅርጽ ፰፻፲፰ ርእሰ ሀባይ የሚባሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ ጌጥ አድርገው ውስጡዋን በወርቅና በእንቍኢ አስጌጠዋል ውጭዋንም ልዩ ሕብረ ቀለም ባላቸው እብነበረዶች፣ የመላእክትና የእንስሳት ሥዕላዊ ቅርጾች አስጊጠው የመጀመርያይቱን ቤተ ክርስቲያን በማይናወጥ ዓለት ላይ መሥርተዋታል።

በሌላ አቅጣጫም ቅድመ ክርስትና ጀምሮ ሐውልቶችን ቀርጾ የመትከል፣ ታላላቅ ቤተ መንግሥቶችን መቃብረ ነገሥታትን በማነጽ፣ ከብረት፣ ከነሐስ፣ ከመዳብ፣ ከወርቅና ከአልማዝ ከመሳሰሉትም ከቡራት ማዕድናት እያነጠሩ ቤተ መንግሥትን የማስዋብና፣ የማስጌጥ ጥበብ ዳብሮባት በነበረችው የአክሱም ከተማ በይበልጥ የሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብ ምንጭ የሆነው የክርስትና እምነት ከገባበት ዕለት ጀምሮ አቡነ ሰላማ ከእስክንድርያ ይዞአቸው የመጡ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የንዋየ ቅድሳት ዓይነቶችን መሠረት ያደረጉ የዕደ ጥበብና የሥነ ጥበብ እውቀት በይበልጥ እያደገና እየዳበረ ስለሄደ አዲሲቱ ቤተ ክርስቲያ ናችን እፁብ ድንቅ የሚባልላቸው ሃይማኖታዊ ቅርሶች ባለቤት ለመሆን በቅታለች።

የክርስቲያን ደሴት በመባል የምትጠራው ሀገራችን የቅድመ ታሪክና የታሪክ ዘመን ቅርሶች ሙዜየም በመባል የምትታወቀው ፺፱% ያህሉ ራስዋን ቤተ ክርስቲያናችንንና የቤተ ክርስቲያን ቅርሶችን የሚመለከት ነው።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሁለት ሺህ ዘመናት የክርስትና ታሪኩዋ በቅርስነት የምንጠቅሳቸው:-

ሀ. ከዓለት ተፈልፍለው የታነፁ አቢያተ ክርስቲያናት

ለ. ከጥርብ ድንጋይ የታነፁ አቢያተ ክርስቲያናት

ሐ. ቅዱሳት የብራና መጻሕፍት

መ. የቤተ ክርስቲያን ባለ መጾር መስቀሎች

www.ethiopianorthodox.org

ሠ. የጳጳሳትና የካህናት የእጅ መስቀሎች

ረ. ከእብነ በረድና ከዕፅ የተቀረፁ ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳት

ሰ. የቁርባን ጻሕልና ፅዋዕ

ሸ. የሕጽበት ሰንና ብርት

ቀ. የዝማሬ ከበሮ፣ ፅናፅልና መቋሚያ

በ. አዋጅ መንገሪያና መጥሪያ ደውልና ቃለ አዋዲ (ቃጭል)

ተ. ልብሰ ተክህኖና ጽንሐሕ

ቸ. መሰበ ወርቅና ማኅተም

ነ. የወግና የባሕል ዕቃዎች ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበትና በቅርስነት ስትጠብቃቸው የኖሩና ያሉ ቅርሶች ናቸው።

## ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን

ቅዱሳን ነገሥት አብርሃ ወአጽብሃና አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን በእብነ በረድና በግራናይት ድንጋይ አንጸው በወርቅና በእንቍ አስጊጠው ከጨረሱ በኋላ ከመናገሻ ከተማቸው አክሱም እየተነሱ መጀመርያ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫና ቀጥሎ ወደ ሰሜን አቅጣጫ፣ አከታትለውም ወደ ደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ አቅጣጫ በመንቀሳቀስ ኢአማንያትን በማስተማር በማጥመቅና አዳዲስ አቢያተ ክርስቲያናትን በማነጽ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳትን በመስጠት ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት በጥርብ ድንጋይ ያነጽዋቸው አብያተ ክርስቲያናት በዘመናችን በቅርስነት ባይገኙም ከማይናወጥ ዓለት ፈልፍለው ያነፁዋቸው አብያተ ክርስቲያናት ግን ተራሮችን ተገን አድርገው በደንና በጥሻ ተሸፍነው ከጠላት አደጋ ያመለጡት የአብርሃ ወአጽብሃና ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ዘመን ሕንጻዎች:-

- የአብርሃ ወአጽብሃ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ዓይባ ገማድ
- የውቅሮ ቅዱስ ቂርቆስ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ጽራዕ
- የሚካኤል አምባ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አጽቤ ወንበርታ
- የውቅሮ ማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አምባሰነይቲ

www.ethiopianorthodox.org

- የጉልብሻ ማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ገረዓልታ
- የሀውዜን ተክለ ሃይማኖት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሐውዜን
- የማርያም በራቂት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ገርዓልታ
- የደብረ ማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ተምቤንና

የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት፣ ሦስት ቤተ መቅደስ፣ በርከት ያሉ አዕማደ ሆጻዎች፣ ቀስተ ደመናዊ መስቀሎች፣ የአክሱም ሐውልትን በር የመሰሉ መግቢያ በሮች በልዩ ሀረግና ቅርጽ የተቀረፁ ጣሪያና ግድግዳዎች ተበጅተውላቸው በዘመናችን የዓለም ታሪክ ተመራማሪዎችንና የሀገር ጐብኝዎችን ዓይነ ሕሊና የማረኩ የቤተ ክርስቲያናችን ተቀዳሚ ቅርሶች ናቸው።

ከዘመነ አብርሀ ወአጽብሐ ፫፻፶፮–፬፻፸፩ ዓመተ ምሕረት ድረስ ባለው ጊዜ የነገሡ ነገሥታት ይሁኑ በዚያን ጊዜ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ያደረጉት ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ በታሪክ ጐልቶ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ከ፬፻፸ ዓ.ም ወዲህ ግን በአጼ አልዓሜዳ ዘመነ መንግሥት ተሰዓቱ ቅዱሳን የተባሉ መነኰሳት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከነገሥተ አክሱም አጼ አልአሜዳ፣ አጼ ካሊብ፣ አጼ ገብረ መስቀል ጋር ሰምና ወርቅ ሆነው ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ኢአማንያንን በማጥመቅ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጐም፣ አዳዲስ ገዳማትን በመመሥረት ታላላቅ ክርስቲያናዊ ሥራዎችን በመሥራታቸው ከዓለት ተፈልፍለው የታነፁ አብያተ ክርስቲያናት ይሁኑ ከጥርብ ድንጋይ የታነፁ ገዳማት በርከት ያሉ ቢሆኑም እስከ አሁን ድረስ መሠረታቸው ያልጠፋ፣

- ሚካኤል አፎይ በአክሱም ዳዲ ከልተ
- እንዳ ሰምዖን በአክሱም ዳዲ ከልተ
- ቤተ ጊዮርጊስ በአክሱም ደብረ ማከዳ
- ኢዮራዊ ሚካኤል በጀራዊ ፍልፍሌ
- ደብረ ቈናጽል አባ ሊቃኖስ አክሱም
- እንዳ ቂርቆስ መላዘ ደጌ
- እንዳ ቂርቆስ አጉላል

www.ethiopianorthodox.org

አጼ ካሌብ ከኢትዮጵያ ወደ የመን ሄዶ ሀገረ ናግራን በተባለ ቦታ ያነፀው ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ወቅት መሠረተ ፕላኑና ዓምደ ወርቁ ያልጠፋ ቤተ ክርስቲያንና የመሳሰሉት ሲሆኑ ሕንጻ ቤተ መቅደሳቸው ሳይፈርስ እስከ ዛሬ ድረስ የሚቀደስባቸው ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ:-

- ደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ
- ዛሪማ ጊዮርጊስ አጽቢ ደራ
- ቂርቆስ እጽቢ ደራ

ብቻ ለአብነት የተረፉ ሲሆኑ ከዓለት ተፈልፍለው ከታነፁት የዘመኑ አብያተ ክርስቲያናትም ዋና ዋናዎቹ:-

- ድጉም ሥላሴ በአጼ ካሌብ የታነፀ
- ድጓ ጊዮርጊስ በአጼ ገ/መስቀል የታነፀ
- አቡነ ይምዓታ በአቡነ ብንያም የታነፀ
- ደብረ ሰላም ሚካኤል በአጼ ገ/መስቀል የታነፀ

እንዳ አባ ዮሐኒ በአጼ ገብረ መስቀል የታነፁ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት የቅድመ ዮዲት ጉዲት የጥፋት ዘመን ታላላቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕንጻ ቅርሶች ናቸው።

ከላይ በመጠኑ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው በተሰዓቱ ቅዱሳን አማካይነት የተመሠረቱት እናት ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ቅድምና እንዳአላቸው የሚያጠራጥር ባይሆንም ቅዱሳን ነገሥት አብርሀ ወአጽብሐና ከሣቴ ብርሃን ሰላማ በወርቅና በእንቊ ያነጽዋትን ገበዝ አክሱምን ጨምሮ እስከ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የታነፁት አብያተ ክርስቲያናት ከላይ ከተጠቀሱት ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት በስተቀር በዓይን የሚታይ፣ በእጅ የሚጨበጥ የሥነ ጥበብ ቅርስነት ይዞ የተገኘ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን አልተገኘም።

የኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚያረጋግጠው ከ፰፻፵፪–፰፻፹፪ ዓ.ም ድረስ በነበረው ፵ ዓመት ፈላሻዋ ዮዲት ጉዲት የገነነችበት ዘመን ስለ ነበርና በዚህ ዘመን ክልል የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትና የንዋያተ ቅድሳትን ብዛትና ዓይነት፣ የጠፋውንና የተቃጠለውን የኦርቶዶክስ ቤተ

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ሀብትና ንብረት፣ የታረዱትንና የተሰደዱትን ክርስቲያኖች፣ ቁጥር የሚያረጋግጥ የምርመራ ማስረጃ ባይገኝም ከብዙ የታሪክ ምንጮች እንደሚረጋገጠው አብያተ ክርስቲያናት ከሰሜን ኢትዮጵያ እስከ ደቡብ ኢትዮጵያ ጠረፍ ታንጸው እንደ ነበርና ክርስቲያናዊ እምነት በደበልጥ ተስፋፍቶና ሥር ሰዶ እንደነበር በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች አካባቢ እንደ ዙዋይ ደሴቶችና በጋሞጐፋ ብርብር ማርያም አምባዎች ላይ የተገኙ ክርስቲያናዊ ቅርሶች ለዚህ እንቅስቃሴ ጠቃሚ ማስረጃዎች ናቸው። ከዮዲት ጉዲት ሕልፈት በኋላ ግን በላስታ አምባ ምድሮች አንድ ሌላ አዲስ ክርስቲያን መንግሥት ነገደ ዛጓዬ በመነሳቱ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የአዲስ ዓይነት ሕንጻ ጥበብንና የረቀቀ የሥነ ጥበብ ሥልጣኔ የተላበሱ ሕንጻዎችን ይዛ ብቅ ብላለች።

ይኸውም በሮሐ ላሊበላ እሳት ወለድ ቀይ ዓለት ላይ ከላይ ወደታች እየተፈለፈሉ የታነፁት አስራ ሰባቱ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት:-

- ቤተ ማርያም – ቤተ መድኃኒ ዓለም
- ቤተ አማኑኤል – ቤተ ገብርኤል
- ቤተ ሊባኖስ – ቤተ መርቆሬዎስ
- ቤተ ጊዮርጊስ – ቤተ ጐልጐታ
- አሸተን ማርያም – መካነ መድኃኒ ዓለም
- ገነተ ማርያም – ይምርሃነ ክርስቶስ
- ነአኩቶ ለአብ – ብልብላ ጊዮርጊስ ወዘተ.

የመሳሰሉት ሕንጻዎች ከ፲፩ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ባለው የዘመን ክልል ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ተሐድሶ ያደረገችበት ዘመን እንደ ነበር የሚያረጋግጡ የቅርሶቻችን ሁሉ አንፀባራቂ ከዋክብት ናቸው ለማለት ያስደፍራል። ከላሊበላ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የተከሰተው የግብረ ሕንጻ ጥበብ አብያተ ክርስቲያናትን ከዓለት እየፈለፈሉ ማነጽ በሥዕልና በሐረግ ቤተ መቅደሳቸውን ማስዋብና ማስጌጥ መጻሕፍትን መድረስ፣ መተርጐምና መጻፍ ሥዕል መሣል የመሳሰሉት ጥበባት በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ እስከ ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ እንደ ቀጠለ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

ምንም እንኳን የጥበብ ተሐድሶ ያደረገው የዛጉዬ ሥርወ መንግሥት ተለውጦ ወደ ሰሎምናዊ ሥርወ መንግሥት ሽዋ ቢዛወርም የሥልጣን እንጂ የሃይማኖት ለውጥ ስለ አልነበረ ከላሊበላ ዘመን መንግሥት እስከ ጐንደር ዘመነ መንግሥት በነገሡ ነገሥታትና በየገዳማቱ በተነሱ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አማካይነት በእነ አብርሀ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት የተቋረጠው ቤተ ክርስቲያንን ከዓለት ፈልፍሎ የማነጽ ጥበብ እንደ ገና ከሰሜን ኢትዮጵያ እስከ ደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ ተፋፍሞ በጥቅሉ ከ፪፻ ያላነሱ አብያተ ክርስቲያናት ከዓለት ተፈልፍለው ሲታነፁ ከነርሱ ጐን ለጐን አብሮም ቤተ ልሔምን፣ ቤተ ማኅበርን፣ ዕቃ ቤትን፣ ቤተ መነኰሳትን፣ መቃብረ አበውን አብሮ ከአለት ፈልፍሎ በማነጽ ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በግብረ ሕንጻ ቅርስ አንደኛ ደረጃ እንድትይዝ አድርጓአታል።

እንደነ አብርሀ ወአጽብሐና ከሣቴ ብርሃን ሰላማ፣ አጼ ላሊበላና ነአኩቶ ለአብ ይምርሃነ ክርስቶስ ግብረ ሕንጻ ሁሉ ከ፲፫ኛው እስከ ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሱት ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ካነፁአቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል ስማቸውና ያነፁአቸው አብያተ ክርስቲያናት ዝርዝር በዋነኛነት የሚታወቅ አቡነ አብርሃም ዘገረዓልታ የተባሉ አባት:-

፩. ኢየሱስ ጣሺ ሠሀርቴ
፪. ሚካኤል ዐቢይ ዓዲ ገርዓልታ
፫. ቀመር ፬ቱ እንሰሳ ገርዓልታ
፬. ሚካኤል ምንዳዕ ገርዓልታ
፭. ዮሐንስ ማይኑዲገርዓልታ
፮. ሚካኤል ሞልሀይ ዘንዘንጊ ጻዕዳ አምባ
፯. መድኃኒዓለም ዓዲቃሾ ዓዕዳ አምባ ሲሆኑ ፰ኛው ግብረ ሕንጻ

በመጨረሻ ዘመናቸው ያነፁት መካነ መቃብራቸው ደብረ ጽዮን አቡነ አብርሃም የተባለ የዘመናችን ዕፁብ ድንቅ ቤተ ክርስቲያን ነው።

ከአቡነ አብርሃም ሌላ ልዩ ልዩ ቅዱሳን በየዘመኑ ተነሥተው ያነፁዋቸው:-

፩. አቡነ ገ/መስቀል አይረፍዳ ቅድስት ማርያም ገርዓልታ

www.ethiopianorthodox.org

፪. ደብረ መዓር ጊዮርጊስ ገርዓልታ
፫. አቡነ ሮማኖስ ደብረ ማህል 4ቱ እንሰሳ ገርዓልታ
፬. አላል ደብረ አውጫ ገርዓልታ
፭. ደብረ ማህል ሥላሴ ገርዓልታ
፮. አቡነ ገ/ሚካኤል ቆርቆር ደብረ ማርያም ገርዓልታ
፯. አቡነ ዳንኤል ወቋን ገብርኤል ተንቤን
፰. አቡነ አሮን ዘመቂት ድራንባ ሥላሴ ተንቤን
፱. እንዳማርያም ሕብዕቶ ተንቤን
፲. አቡነ አሮን ዘካርት መቂት
፲፩. አባ ሊባኖስ ደረቃ አባ ሊባኖስ አክሱም
፲፪. ደብረ አቡነ ሙሴ የድባ ማርያም ዳውንት

እንደ አነፁ በየቅዱሳኑ ገድልና በምርምር ከተደረሰባቸው ማስረጃዎች ተረጋግጦአል።

ከላሊበላ እስከ ግራኝ ወረራ ባለው የ፭፻ ዘመናት ክልል አብያተ ክርስቲያናትን ከዓለት ፈልፍሎ የማነጽ ብቻ ሳይሆን ከጥርብ ድንጋይም እፁብ ድንቅ የሚባልላቸው አብያተ ክርስቲያናትን አንበሳ ውድም ካነፀው ባለ ሦስት ቤተ መቅደስ የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን አንስቶ በመላው ትግራይ ኤርትራ፣ ወሎ፣ ጐንደር፣ ጐጃምና ሸዋ በርከት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ታንጸው ስለ ነበር እንደ ዮዲት ጉዲት ዘመን ጣርያቸው በእሳት ግንቦቻቸው በመዶሻ ተደምስሰው ቢጠፉም የዚህ ዘመን ተረፈ እሳት ሆነው ለቅርስነት የተረፉ:-

- አጼ አምደ ጽዮን ያነፁዋት ባለ ፲፪ ቤተ መቅደስ ናዝሬት ቅ/ማርያም
- ወጀራት እንደ አቦና
- አዘቅተ ጥበብ ቤተ ልሔም
- የደቂቀ እስጢፋኖስ መነኩሳት ያነፁዋት ባለ ፰ ቤተ መቅደስ
- ጉንዳጉንዲ ማርያም
- ጣና ቂርቆስ
- አባ ገብረ ክርስቶስ ወልደ ይኩኖ አምላክ ያነፁዋት ባለ ፲፪ ቤተ መቅደስ
- ደብረ ዳግና

www.ethiopianorthodox.org

አቡነ ቶማስ የተባለ የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ራድዕ ያነጻት ባለ ፲፮ መቅደስ ሰላምጌ ማርያም፣ አጼ ናዖድ ያነፃት ዘመዶ ማርያም እስከነ ሥዕልዋ የጉጃም መርጡለማርያም ፈራርሶ የሚታይ ሕንጻ የመሳሰሉት አብያተ ክርስቲያናት የቅድመ ግራኝ ከጥርብ ድንጋይ ተገንብተው እስከ ዘመናችን የደረሱ የግብረ ሕንጻ ቅርሶች ናቸው።

## ሥዑላን አብያተ ክርስቲያናት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሲ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትደነቅባቸው ጥበቦችዋ ሁሉ ሃይማኖታዊ የሥነ ጥበብ ቅርስዋ በመሆኑ በዘመነ ኦሪት የተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍትና መቅደሰ ኦሪት ባይገኙም በጥንታዊያኑ ሐውልቶቻችን ተቀርፀው የሚታዩት ጥበባዊ ሠራዊት አምልኮተ እግዚአ ብሔር ካደረበት መንፈሰ ሕሊና የፈለቁ መሆናቸውን ያስገነዝቡናል።

ይሁን እንጂ ከዓለት ተፈልፍለው ከታነፁት አብያተ ክርስቲያናት ቅድስተ ቅዱሳንና ቤተ መቅደስ ገጽ ላይ ተሥለውና ተቀርጸው ከሚታዩት ሃይማኖታዊ የጥበብ ሥራዎች ባህልንና ሃይማኖትን፣ ታሪክን፣ ማኅበራዊ ኑሮን የሚያንጸባርቁና የሚያስተምሩ በመሆናቸው ከሁሉም በላይ ክብርና ጥንቃቄ የተሞላበት አያያዝና እንክብካቤ የሚገባቸው ዕፁብ ድንቅ ቅርሶች ናቸው።

በቅድመ ግራኝ ወረራ ከታነፁት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ጥቂቶች ብቻ ለአብነት ከሚጠቀሱት መካከል፣

| | |
|---|---|
| የላሊበላ ቤተ ማርያም | አሸተን ማርያም |
| ገነተ ማርያም | ዋሻ ሚካኤል |
| ደብረ ጽዮን አቡነ አብርሃም | ጉሕ አቡነ ዳምዓታ |
| ማርያም በራቂት ገርዓልታ | ውቅሮ ቂርቆስ ዕራዕ |
| ዘመዶ ማርያም ላስታ | ደብረ አቡነ ሙሴ ዳውንት |
| ደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ | ዘሪማ ጊዮርጊስ |
| አግቦ ቂርቆስ | |

የመሳሰሉት በመላዕከት በቅዱሳን፣ በድንግል ማርያም፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ተአምር ሥዕልና ሐረግ የተዋቡና የተጌጡ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ አብዛኛዎቹን ሥዑላን አብያተ ክርስቲያናት የግራኝ እሳት በአልቶአቸው ቀርቶአል።

www.ethiopianorthodox.org

በሌላ አንጻር ግን ከ፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በይበልጥም ጐንደር የኢትዮጵያ መናገሻ ከሆነችበት ዘመን አንሥቶ እያንዳንዱ ንጉሥ መስፍንና ሀገረ ገዥ፣ ኢኮኖሚው የፈቀደለት ኅብረተሰብ፣ በየከተ ማውና በየገጠሩ በየገዳማቱ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ከጥር ድንጋይ በማነጽ ቅድስተ ቅዱሳንንና ቤተ መቅደሳቸውን በሙሉ አርቶዶክሳዊ የሥነ መልእክት ምሥጢርንና ቅዱሳት መጻሕፍት ምንጭና መሠረት ያደረጉ ምርጥ ታሪኮችን በመሳል:-

| | |
|---|---|
| ትንቢተ ነቢያትን | ወንጌልን |
| ገድለ ሰማዕታትን | ገድለ ሐዋርያትን |
| ተአምረ ማርያምን | ጸሎተ ቅዱሳንን |
| አሠረ ነገሥትን | ተአምረ ኢየሱስን |

ቀምሮ በመሳል በመላ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ያሸበረቁና ያበቡ ሲሆን በአጠቃላይ እስከ ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በርከት ያሉ ሥዑላን አብያተ ክርስቲያናት እንደሚገኙ ጥናታዊ መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

በዚህ መሠረት ስማቸው ሳይጠቀስ የማይታለፉ ሥዑላን አብያተ ክርስቲያናት በልዩ ልዩ አደጋ የተቃጠሉትን ትተን:-

- የጐርጐራ ደብረ ሲና ማርያም
- የጐንደሩ ደብረ ብርሃን ሥላሴ
- የጣናው ክብራን ገብርኤል
- የጣናው ናርጋ ሥላሴ
- የእንደርታው ደ/ምሕረት ጨለቆት ሥላሴ
- የደርስጌ ማርያም
- የተንቤኑ ደብረ ግንፋይ ሥላሴ ገዳም
- የዓድዋው ደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም
- የእንድርታው ደብረ መዊዕ ሚካኤል
- የቤገምድሩ ደብረ ታቦር ኢየሱስ የጋይንትዋ ቤተልሔም ማርያም
- የዋድላው የነጃ ሚካኤል
- የወሮሂመኑ ተንታ ሚካኤል

www.ethiopianorthodox.org

- የደሴው ደሴ መድኃኔ ዓለም
- የየጁ መርጦ ኢየሱስ
- የጐጃሙ ዲማ ጊዮርጊስ
- የዘጌይቱ ውራ ኪዳነ ምሕረት
- የአዲስ አበባዋ እንጦጦ ማርያም
- የአዲስ ዓለምዋ ቅድስት ማርያም
- የምንጃር ሸንኮራ ባልጪ አማኑኤል
- የወረ ኢሉ መካነ ሥላሴ
- የሸዋ አንኮበር መ/ዓለም
- የሸዋ ድንበር ማርያም
- የአዲስ አበባው መካነ ሥላሴ
- የጐንደር ማኅደረ ማርያም
- የመንዝ ደብረ ማርያም
- የጐጃም ደብረ ማርቆስ
- የእንጦጦ ራጉኤል
- የከፋው አንደራቻ መ/ዓለም
- የፍቼ ጊዮርጊስ

ለአብነት ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ዕፁብ ድንቅ የሚባልላቸው ሥውላን አብያተ ክርስቲያናትና የሥነ ጥበብ ታሪክ ተመራማሪዎችን የማረኩ ምርጥ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው:-

## ቅዱሳት መጻሕፍት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እጅግ በጣም ከሚደነቁበትና ከሚመሰገኑበት አንዱና ዋንኛው ከእንሰሳት ቆዳ ብራና አውጥቶ፣ አድምቆ ቀርጾና አሳምሮ ጥራዛተ መጻሕፍት ማዘጋጀት ድንጋይ ደቁሶ፣ አፈር አንጥሮ ሥራ ሥር አበባና ቅጠላ ቅጠል ቀምሞ፣ የእህል ዘሮችን አሳርሮ ልዩ ልዩ ኅብር ያላቸው ቀለማ ቀለማትን በማውጣት ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጻፍና በመሳል በረጅም ጊዜ ጥረትና በሰፊ ትዕግሥት ያበረከቱልንን ቅርስ በአኀዝ ለመግለጽ የሚቻል አይደለም።

www.ethiopianorthodox.org

በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ ገዳማትና አድባራት የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በየዕቃቤቶቻቸው ውስጥ በክብርና በጥንቃቄ ተይዘ ውና ተጠብቀው የሚገኙ የቅዱሳት መጻሕፍት ቅርሶች የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የደለበ የቅርስ ባለቤትነትን የሚያስመሰክሩ ናቸው።

የብራና ቅዱሳት መጻሕፍትን በሁለት ክፍሎች መድበን ልናያቸው ይገባል ይሔውም ከሥነ ጥበብ ቅርስ ትርጓሜ አንጻር በሥዕልና በሀረግ ያሸበረቁ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ሥዕልና ሐረግ የሌላቸው የብራና መጻሕፍት ናቸው። ሁለቱም የመጻሕፍት ዓይነቶች የቤተ ክርስቲያኒቱ የባሕልና የሃይማኖት መሠረታዊ ቅርሶች ቢሆንም በይበልጥ ግን ሥዕልና ሐረግ ያላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ ሥራንና ሃይማኖታዊ መሥዋዕትነትን በግዙፍ ሥዕላዊ መግለጫ ስለሚገልጹ የሊቃ ውንቶ ቻችን እጥፍ ድርብ ጥበብንና የአእምሮ ብስለትን የሚመሰክሩ ስለሆኑ በቅርስነታቸው እጥፍ ድርብ ዋጋና ክብር ያላቸው ናቸው።

የቤተ ክርስቲያናችንን ቅዱሳት መጻሕፍት ብዛትና ዓይነት በአኀዝ ለይቶ ለመግለጽ እጅግ በጣም አደጋች ቢሆንም በሀገራችን እስከ አሁን ድረስ በተደረገው ጥናትና ምርምር በብራና ላይ ተጽፈው ለብዙ ዘመናት አገልግሎት ላይ የዋሉ አርእስተ መጻሕፍት ከ፰፻፶ በላይ እንደሆነ ልዩ ልዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

እነዚህ የብራና መጻሕፍት ብሉያትንና ሐዲሳትን፣ መጻሕፍተ ሊቃውንትን፣ ገድላትን፣ ድርሳናትን የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍ ትን፣ መልክአ መልክእን የአርት መደብላትን የፍልስፍናና የባሕረ ሀሳብ ትምህርትን የመሳሰለውን ሁሉ አጠቃለው የያዙ መጻሕፍትን ሊቃው ንተ ቤተ ክርስቲያን በተለያየ አቅጣጫ ሲጠቀሙባቸው ኖረዋል።

ከነዚህ ሁሉ ግን የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ወንጌለ መንግሥትን ለመስበክና ለማስተማር የቅዱሳን ገድላትንና ተአምራትን ለመግለጽ የአሕዛብን ጨካኝና አረመናያዊ ተግባር ለመፈጸም የተጠቀሙበት ሰማዕታተ ክርስቶስን የማሰቃየት ተግባርና የማሰቃያ ዘዴዎች መሣሪያዎችን በሙሉ የሚገልፁ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በልዩ ልዩ ኅብረ ቀለሞች አስምረው በመሳል በቅዱሳት መጻሕፍት ታሪኮች ላይ ያሰፈሩት ጥበብ ከሁሉም በላይ የሚደነቅ ነው።

በዚህ መሠረት ስለ ኢትዮጵያ ሥነ ጥበብ ቅርስ በተደረገው ጥናትና ምርምር ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሊታውንተ ቤተ ክርስቲያን በሥዕልና በሐረግ ያሸበረቋቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

| | |
|---|---|
| አምስቱ ብሔረ ኦሪት | ድርሳነ ሚካኤል |
| መጽሐፈ ዳዊት | አርጋኖን |
| መጽሐፈ ሄኖክ | ድርሳነ ገብርኤል |
| ደቂቀ ነቢያት | ድርሳነ ፯ቱ እንሰሳ |
| አርባዕቱ ወንጌል | ድርሳነ ራጉኤል |
| ራዕየ ዮሐንስ | ገድለ ተ/ሃይማኖት |
| ገድለ ሐዋርያት | ገድለ ቂርቆስ |
| ሃይማኖተ አበው | ገድለ አረጋዊ |
| ገድለ ሰማዕታት | ገድለ ሳሙኤል ዘዋልድባ |
| ገድለ ቅዱሳን | ድርሳነ ጽዮን |
| ተአምረ ኢየሱስ | ዜና ሥላሴ |
| ነገረ ማርያም | ማኅሌተ ጽጌ |
| ተአምረ ማርያም | ባሕረ ሀሳብ (አውሸኸር) |
| ገብረ ሕማማት | ገድለ ኤዋስጣቴወስ |
| ጠቢበ ጠቢባን | ገድለ መድኃኒነ እግዚእ |
| መድበለ ሃይማኖት | |

የመሳሰሉት ቅድሳት መጻሕፍት በጥንታውያን የኢትዮጵያ ገዳማት ዕቃቤቶች በብዛት ባይሆንም አልፎ አልፎ በአብነትነት በሥዕልና በሐረግ አሸብርቀው የሚገኙ ቅድሳት መጻሕፍት ዓይነተኛ ቅርሶቻችን ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት በሥዕልና በሐረግ ያሸበረቁት ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል እንደ አርባዕቱ ወንጌል ገድለ ሰማዕታትና ገድለ ቅዱሳን፣ ገድለ ሐዋርያት የመሳሰሉ መጻሕፍት ቁጥራቸው እጅግ በጣም ውሱን በሆነ መልኩ በተወሰኑ ጥንታውያን ገዳማት ብቻ ከግራኝ ወረራ በፊት ተጽፈውና ተስለው የተገኙ ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ከግራኝ ወረራ በኋላ ባለው ዘመን እየተጻፉና እየተሳሉ የተሰራጩ ስለሆኑ በብዛትም በዓይነትም በቦታም በርከት ብለው ይገኛሉ።

www.ethiopianorthodox.org

# ለአብነት ለመጥቀስ ያህል

- የ፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአባ ገሪማ ወንጌል
- የ፲ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የላሊበላ ወንጌል
- የ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክብራን ገብርኤል ወንጌል
- የ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የደብረ ወርቅ ወንጌል
- የ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሐይቅ እስጢፋኖስ ወንጌል
- የ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዮሐንስ ከማ ገድለ ሰማዕታት
- የ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዝዋይ ደሴት ገድለ ቅዱሳን
- የ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሸን ማርያም መጽሐፍ ጤፉት
- የ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የጉንዳንጉንዲ መጻሕፍት
- የ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የእንደጨጌ ተአምረ ማርያም
- የ፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የጨለቆት ሥላሴ ሃይማኖት አበው
- የ፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዲማ ጊዮርጊስ ተአምረ ማርያም
- የ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአጼብ ሥላሴ ድርሳነ ሚካኤል
- የ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዋልድባ ተአምረ ኢየሱስ
- የ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የራስ ወሌ ዳዊት ደብረ ዳሞ

የመሳሰሉት ቅዱሳት መጻሕፍት በመቅድማዊ ሀረጋቸው በታሪካዊ አሳሳላቸው በሃይማኖታዊ መግለጫቸው በልዩ ልዩ ኅብረ ቀለም ሥነውበታቸው በየመቶ ክፍለ ዘመኑ የተንፀባረቀው የኢትዮጵያ ሊቃውንት የሥዕል ጥበብ የፊደል ቅርጽና የብራና አወጣጥ ባሕልና ችሎታ ዋነኛ ማስረጃ ሁነው ሊጠቀሱ የሚገባቸው የሥነ ጥበብ ሥራዎች ናቸው።

## የመዶር መስቀልና የእጅ መስቀል

የክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ ጀምሮ በኢትዮጵያ የተነሱ ሰባክያን ወንጌል መነኩሳትና ካህናት በቀኝ እጃቸው መስቀል በግራ እጃቸው

www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፈ ወንጌል አቅፈው በአሪታዊው ሃይማኖትና በበዕድ አምልኮቶ ሥር የነበረውን ሕዝብ እያስተማሩና እያጠመቁ እየባረኩና እያቆረቡ ታላቅ ሐዋርያዊ ተልዕኮአቸውን በመፈጸማቸው ኢትዮጵያን የክርስ ቲያን ደሴት አሰኝተዋታል።

በዚህ መሠረተ ዓላማ መስቀል ለመባሪኪያ፣ ለመቀደሻ ለመሳለም አገልግሎት በሚጠቀሙበት ወቅት አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት በተተከሉ ቁጥር አዳዲስ ካህናት በተሰየሙ ልክ መስቀልና መጽሐፈ ወንጌል የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሣርያ በመሆናቸው በየዘመኑ በተነሡት ጠቢባን እድ አማካይነት እንደየጥበብ ደረጃቸው ከዕፀ ከእብን በረድ ከብረት፣ ከነሐስ፣ ከመዳብ፣ ከብር፣ ከወርቅ ማዕድን አንጥረው በመሥራት ለሃይማኖታዊ ግልጋሎት ስለዋሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት ቀጥሎ በብዛትና በዓይነት በቤተ ክርስቲያን ቅርስነት በየገዳማቱ ተከማችተው ይገኛሉ።

እንደ ሥነ ጥበብ ቅርስ ተመራማሪዎች አገላለጽ በጥንታዊት ኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት ቤተ መዘክር የሚገኙ የመጾር መስቀሎ ችና የዕጅ መስቀሎች በሥነ ጥበባዊ አሠራራቸውና ቅርጻቸው በሦስት ዐበይት ክፍሎች ይመደባሉ:-

ሀ. የዘመነ አክሱም መስቀል ዓይነቶች

ለ. የዘመነ ዛጓ (ላሊበላ) መስቀል ዓይነቶች

ሐ. የዘመነ ጐንደር መስቀል ዓይነቶች

ተብለው በጥናትና ምርምር ተለይተው ተመድበዋል።

ይህም ማለት በየዘመኑ የተሠሩት የመስቀል ዓይነቶች አንድ ወጥ የሆነ ሦስት ዓይነት መልክና ቅርጽ አላቸው ማለት ሳይሆን በተቻለ መጠን የተቀራረበ የጥበብ ሥራ የሚታይባቸውና አንዱ ከአንዱ እጅግ በጣም ርቆ ያልሄደ ልዩነት የሚታይባቸው የመስቀል ዓይነቶች ለማለት ያህል ነው።

www.ethiopianorthodox.org

እነዚህ የመጾርና የእጅ መስቀል ልዩ ልዩ ዓይነት ሥራዎች ከዘመን ርዝማኔ የተነሣ በይበልጥ ደግሞ የዘመነ አክሱም መስቀል ዓይነቶች ለአብነት ያህል በተወሰኑ ገዳማት ብቻ ሲገኙ የተገኙትም ቢሆኑ የቅዱሳን በትረ መስቀልና የእጅ መስቀሎች ለዚያም ከብረት ብቻ የተሰሩት ተገኝተዋል።

የተቀሩት ግን በ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አውሮጳውያን አርኪዎሎጂስቶች በአክሱም፣ በየሃ፣ በጐሎ መኽዳ፣ በመጠራ አካባቢዎች ባደረጉት የአርኪዎሎጂ ምርምር የነገሥታት ማጌጫ የነበሩ በአንገት የሚታሠሩ ባለ ወርቅ ሐብል የወርቅ መስቀሎችና የነሐስ መስቀሎች ተገኝተዋል።

ከዚህ ሌላ ከአብርሀ ወአጽብሐ ጀምሮ በአክሱም የነገሡ ነገሥታት እንደ ንጉሥ ኢዛና፣ አልአሜዳ፣ ካሌብ፣ ገብረ መስቀል፣ አርማህ የመሳሰሉት ክርስቲያን ነገሥታት በአንድ ገጽ የራሳቸውን ምስል በሌላ ገጽ የዘመነ አክሱምን የመስቀል አቀራረጽ ዓይነት የሚገልጹ መስቀሎች ከነሐስ፣ ከመዳብ፣ ከብርና ከወርቅ የተሰሩ መገበያያ ገንዘቦች በብዛት ተገኝተዋል።

በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሱት የላሊበላ መስቀል ዓይነቶች እንደዚሁ ከመቅጽበት የመጡና የተፈሩ ሳይሆኑ በነበረው የመስቀል ዓይነት ላይ መጠነኛ የቅርጽና የዓይነት ለውጥ በማድረግ ራሱን የቻለ የዛጓ ዘመነ መንግሥት መግለጫ ሊሆኑ የሚችሉ መስቀሎች ተሠርተውና ተቀርጸው በአገልግሎት ላይ ውለዋል። እነዚህም የላሊበላ መስቀሎች በሮሐ ላሊበላ ገዳማትና በአካባቢው እንደዚሁም በትግራይ ጥንታውያን ገዳማት አልፎ አልፎ ተገኝተዋል።

በላሊበላ አካባቢ የሚገኙ መስቀሎች ልዩ ስምና አጠቃቀም ባይታይባቸውም በተለይ በትግራይ አካባቢ የላሊበላ መስቀል ዓይነት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት «ነገዲ መስቀል» አልቃሽ መስቀል እያሉ በመጥራት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ሕሙማንን ጸበል ያጠምቁበታል፣ ልዩ ቡሩክ ይሰጡበታል።

www.ethiopianorthodox.org

በሦስተኛ ደረጃ የሚጠቀሱት የጐንደር ዘመነ መንግሥት መስቀሎች መጠናቸው እጅግ በጣም ትልቅ በአብዛኛው ከነሐስ የተሠሩ በላያቸው ላይ የሥነ ስቅለት ሥዕል ምስለ ፍቁር ወልዳ የመላእክትና የቅዱሳን ሥዕል የተቀረጸባቸው ውፍረትና ክብደት ያላቸው ናቸው።

እነዚህ የመስቀል ዓይነቶች ከዮዲት ጉዲትና ከግራኝ አህመድ ወረራ ማግስት የተሠሩ በመሆናቸው የአሠራር ቅርጻቸውም እስከ ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እየተባዛ ስለወጣ በብዛትም ሆነ በዓይነት በሁሉም አካባቢና በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ይገኛሉ። እንዲያውም ከዘመነ መሳፍንት ወዲህ ከብርና ከወርቅ እየተሠሩ ለብዙ ገዳማት ስለተሰጡ ጽሑፍ አንብቦ ካልሆነ በስተቀር በቅርጽ ለመለየት አስቸጋሪ ይሆናል።

ስለሆነም ከዘመነ አክሱም ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ የተሠሩት የመስቀል ዓይነቶች እጅግ በጣም የበዙ በመሆናቸው ኢትዮጵያውያን የሥነ ጥበብና የዕደ ጥበብ ባለሞያዎች የረቀቀ እውቀትና የፈጠራ ችሎታ ብስለት መለኪያና መመዘኛዎች ናቸው እነዚህም የጥንቱና የአሁኑ የጥበብ ቅርሶች በቤተ ክርስቲያን ባለ አደራነት ተጠብቀው የሚገኙ ስለሆነ ቅርስ የእውቀት፣ የጥበብና የታሪክ፣ የባህል ማስረጃ ወይም ትምህርት ቤት ሆኖ ለኅብረተ ሰባችን አገልግሎት ይሰጣል።

## የቤተ ክርስቲያን የቅርሳቅርስ መዘክርነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ጸሎት ብቻ ሳትሆን የባሕል ሙዜምና የጥበብ ቤተ መዘክርም ጭምር ናት።

ይኸውም ነገሥታቱና መሳፍንቱ ከየገዳማቱና አድባራቱ አበምኔቶች መነኰሳት ካህናት ሊቃውንት ሁሉ በነበራቸው ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ትስስር ምክንያት ማዕከላቸውን ቤተ ክርስቲያን አድርገው በግልና በኅብረት በሚያደርጉት ሃይማኖታዊ አስተዋጽኦ ከሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሕንጻት ጀምሮ እስከ ንዋየ ቅድሳት አደረጃጀት በግዴታም በውዴታም በመሳተፍ ቤተ ክርስቲያኒቱን በወርቅና በዕንቍ በብርና

በንሐስ በብረትና በእብነ በረድ የተሠሩ ንዋያተ ቅድሳትና ቅዱሳት መጻሕፍት ባለቤትና ባለንብረት አድርገዋታል፤

ይኸውም:-

ሀ. ነገሥታት ለስማቸው መዘክርያ፤ ለመንግሥታቸው ማመስገኛ ማሞገሻ ቤተ ክርስቲያን እንዲታነጽ በሚያዙበት ወቅት ከልብሰ መንግሥታቸው ጀምሮ ዘውድና የወርቅ ጫማቸው ድረስ ለገዳማት፤ ለአድባራት ቤተ ክርስቲያን ያወርሳሉ።

ለ. መሳፍንት ንጉሡ ላከበረው ገዳም ወይም ደብር ያላቸውን ሽልማትና ጌጥ በሕይወት ዘመናቸው ወይም ሲሞቱ ያወርሳሉ።

ሐ. ነገሥታቱም ሆኑ መሳፍንቱ አንድ አዲስ ቤተ ክርስቲያን በስማቸው ቢያንፁ ወይም ለደብሩ መተዳደሪያ ርስተ ጉልት መገልገያ ንዋየ ቅድሳት በገንዘባቸው ገዝተው እንዲገለገሉ ያደርጋሉ።

መ. የገዳም መነኰሳት የመጻፍና የመደጐስ ችሎታ ስለ ነበራቸው ብራና ፍቀውና ጽፈው ደጉሰው ማኅደር አዘጋጅተው ገዳሞቻቸውን በቅዱሳት መጻሕፍት ንዋየ ቅድሳት ያደራጇሉ።

ሠ. ምዕመናኑ ለሞተ ዘመድ መታሰቢያ ወይም ደግሞ እነርሱ ራሳቸው እንዳንድ ገጸ በረከት መጽሐፍ አጽፈው መስቀል አሠርተው አልባሳት አሰፍተው ለየቤተ ክርስቲያናቸው ይሰጣሉ።

ረ. የገዳሙ ወይም የደብሩ የስዕለት ጥሬ ገንዘብ ወይም ሌላ ሀብትና ንብረት እየተሸጠ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት ሊውል የሚገባው መጽሐፍ ወይም ሌላ ንዋየ ቅድሳት በመግዛት ይጠቀማሉ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል አምስት

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ

ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትናንት የነበረች ዛሬም ያለች ነገም የምትኖር ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ናት። «ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ» ስንል ወቅታዊውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዋን ለመግለጽ እንጂ ጥንታዊ ታሪክና ህልውና ያላትን ቤተ ክርስቲያን አዲስ አድርጐ ለማቅረብ አይደለም።

ቤተ ክርስቲያኒቷ በአሁኑ ጊዜ ህልውናዋን ይበልጥ ለማጠናከርና ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በምታደርገው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ሐዋርያዊ ተልእኮዋን በመወጣት ላይ ትገኛለች። ለታሪክና ለትውልድ የሚተላለፉ ዐበይት የሥራ ክንውኖችንም በማስመዝገብ ላይ ናት።

ይህች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ወቅቱ የሚጠይቀውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በሚገባ መወጣት የሚቻለው የቤተ ክርስቲያን አበውን ቁጥር በማበርከትና አህጉረ ስብከትን በማስፋፋት፣ መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን በመክፈትና የነበሩትን በማጠናከር በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተሟላና ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸው መምህራንን በዘመናዊ የስብከትና የአስተዳደር ዘዴ እያሰለጠኑ መላክ፣ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር መጻሕፍትን በዓይነትና በብዛት እያዘጋጁ ማሠራጨት መሆኑን ተገንዝባ ደረጃ በደረጃ የምታከናውናቸው ተግባራት በጉልህ እየታዩ ነው።

## ሢመተ ጳጳሳት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከት በመላው ሀገሪቱ የአስተዳደር መዋቅር የተዘረጉ ናቸው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ያልደረሰችባቸው አካባቢዎችና የማትዳስሳቸው ጠረፎች አይገኙም፣ ተከታዮቿ ምእመናን ባሉበት ቦታ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ትኖራ

www.ethiopianorthodox.org

ለች በሌሉበት አካባቢም ቢሆን ትምህርተ ወንጌልን ማስተማርና አማንያንን ማፍራት ሐዋርያዊ ግዴታዋ ነው። የአብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና እያደገ የሚሄደውም ከዚህ የተነሣ ነው።

አህጉረ ስብከት እየሠፉ፣ የአብያተ ክርስቲያናትና የምእመናን ቁጥር እያደገ በሄደ መጠንም የቤተ ክርስቲያን አባቶችንና መምህራን ወንጌልን ማብዛት ዓይነተኛ ተልእኮዋ ነው።

በዚህም መሠረት በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባቶች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ቁጥር ፴ ሲሆን፣ በሀገሪቱ መንግሥታዊ አስተዳደር መዋቅር በተዘረጉት ክልሎች በውጭው ዓለም ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተከታዮች አበውን መመደብና አዳዲስ መንበረ ጵጵስናዎችን መክፈት ግዴታና አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

፩. ቀደም ሲል በአፍሪካ፣ በኢየሩሳሌም፣ በምዕራብ አገሮችና በካሪቢያን ደሴቶች ተልከው አገልግሎት ሲሰጡ ከነበሩት ቆሞሳት:-

ሀ. በአውሮጳ

ለ. በካሪቢያን ደሴቶችና በላቲን አሜሪካ

ሐ. በአፍሪካ

መ. በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት በጥር ወር ፲፱፻፹፭ ዓ.ም አራት ጳጳሳት፣

፪. ኅዳር ፬ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም.

ሀ. ለጋምቤላ

ለ. ለድሬዳዋ

ሐ. ለኢሉባቦር

መ. ለደቡብ ኦሞ

ሠ. ለምዕራብ ሐረርጌ

www.ethiopianorthodox.org

ረ. ለምሥራቅ ሸዋ

ሰ. ለከምባታ ሐድያና ጉራጌ አህጉረ ስብከት ሰባት ጳጳሳት በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ ተሾመዋል።

መንፈስ ቅዱስን መሪ አድርጐ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ርእሰ መንበርነት የሚሠራው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የበላይ ኃላፊና ወሳኝ አካል ነው።

ቅዱስ ሲኖዶስ በየዓመቱ ሁለት ጊዜ በምልዓት እየተሰበሰበ በተላላቅ ጉዳዮች ላይ በመወያየት የቤተክርስቲያኒቱን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሥራዎች ይመራል፣ ይሠራል ያሠራል በየዓመቱ መጀመሪያ ጥቅምት ፲፪ እና በርክበ ካህናት ትንሣኤ በዋለ በ፳፭ኛው ቀን በምልዓት የሚ ሰበሰበው ጉባኤ ተወያይቶ የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎችና የሚያወጣቸው መመሪያዎች ከመንበረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ ጽህፈት ቤት ጀምሮ በየአህጉረ ስብከቱ ሥራ ላይ መዋላቸውን በበላይነት የሚከታተል በየዓመቱ የሚከናወኑ ተግባራትን እየመረመረ በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚሰጥ ቋሚ ሲኖዶስ አለ። አስቸኳይና አስፈላጊ የሆኑ ተግባራት ሲያጋጥሙ ቅዱስ ሲኖዶሱ በምልዓት ሊሰበሰብ ይችላል።

ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር የሚመራው ቅዱሳን አበው ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በወሰኑት ፍትሕ መንፈሳዊ ነው። እምነቷንና ሥርዓቷን የሚያስጠብቀው ራሱን ችሎ በተዘጋጀ ቀኖና መሠረት ነው።

ይህንኑ ቀኖናዊ አስተዳደር ተግባራዊ በማድረግ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለዘመናት ከቆየው መንግሥታዊ የአስተዳደር መዋቅር ነጻ ሆና ራሷን በራሷ በመምራት ላይ ትገኛለች።

በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ አስተዳደር የሚመራው በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የበላይነት ከሊቃነ ጳጳሳቷ መካከል በቅዱስ ሲኖዶስ በተመረጠ ሊቀ ጳጳስ ሥራ አስኪያጅነት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያኒቷ በአሁኑ ጊዜ በተቀዳጀችው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በመጠቀምና ቀደም ሲል ሲሠራበት የነበረውን ሕገ ቤተ ክርስቲያን በማሻሻልና ከጊዜው ጋር የተገናዘበ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች (ሠራተኞች) መተዳደሪያ ደንቦችን በማውጣት በሥራ ላይ እንዲውሉ አድርጓል። የቤተ ክርስቲያኒቱ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር መመሪያ የሆነውም ሆኗል ቃለ ዐዋዲ ወቅቱን ተከትሎ እንዲሻሻል አድርጓል።

- ባለፈው ሥርዓት የተወረሱት የቤተ ክርስቲያን የገቢ ምንጮች የነበሩ ቤቶችና ንብረቶች፤
- የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ምንጮች የሆኑት መንፈሳዊ ኮሌጅን የመሳሰሉት መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶች እንዲመለሱ አድርጓል።
- ለሌላ ይዞታ ውለው የነበሩ የቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረትና አፀደ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ብርቱ ጥረትና በኢሕድሪ መንግሥት በጎ ፈቃድ ወደቀድሞ የቤተ ክርስቲያን ይዞታነታቸው ተመልሰዋል።

ቅዱስ ሲኖዶስ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት የሚተከሉባቸውን ቦታዎች በሕግ እያስፈቀደ ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርጓል። እንደባሕረ ጥምቀትና መስቀል አደባባይ የመሰሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበዓላት ማክበሪያ ቦታዎችም በየሥፍራው እንዲከበሩ አድርጓል።

## ስብከተ ወንጌል

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ስብከተ ወንጌል የቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረት መሆኑን ተገንዝበው ከሁሉም በላይ ለትምህርተ ወንጌል ቅድሚያ በመስጠት ከአዲስ አበባ ጀምሮ በየአህጉረ ስብከቱ ያለዕረፍት በመዘዋወር ወንጌለ መንግሥትን ይሰብካሉ በየአህጉረ ስብከቱ የሚገኙ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትም ይህንኑ የቅድስና ፈለግ በመከተል በየአውራጃውና በየወረዳው እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ሐዋርያዊ ተልዕኮዋቸውን በመፈጸም ላይ ይገኛሉ፤ በየሥፍራው የተመደቡ ሰባክያነ ወንጌልም የቅዱስ ፓትርያርኩንና የብፁዓነ ሊቃነ ጳጳሳቱን አሠረ ጽድቅ በመከተል ሐዋርያዊ ግዳጃቸውን እየተወጡ

www.ethiopianorthodox.org

ናቸው። ከዚህም የተነሣ በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያት እግሮች ያልተረገጠ የኢትዮጵያ አካባቢ አይገኝም። ትምህርተ ወንጌል በቃልም በጽሑፍም በስፋት እየተሠራጨ ነው። በገጠርም ሆነ በከተማ በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት በየዕለቱ የስብከተ ወንጌል መርሐ ግብር ተዘርግቶ ምእመናን ትምህርተ ወንጌልን በመመገብ ላይ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ «ውስተ ኵሉ ምድር ወጽአ

ነገሮሙ ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ

ድምፃቸው በምድር ሁሉ ላይ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ (መዝ.፲፰.፬) የተባለው ቃለ መጽሐፍ በተግባር በመፈጸም ላይ ይገኛል።

## ሰበካ ጉባኤ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደረው ከሐዋርያት ተያይዞ በመጣው የማኅበረ ካህናትና ምእመናን የአንድነት ጉባኤ ነው። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በመላ ሀገሪቱ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በሰበካ ጉባዔ ተደራጅተዋል። ካህናቱም ሆኑ ምዕመናኑ የሚመሩትና የሚተዳደሩት በቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት ነው። በመላ ሀገሪቱ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የተዘረጋውን የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ለማጠናከር በሁሉም አህጉረ ስብከት በየጊዜው ሥምሪት ይደረጋል ትምህርታዊ ሴሚናር ይሰጣል። በየዓመቱ አንድ ጊዜ በመንበረ ፓትርያርኩ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ርእሰ መንበርነት በሚደረግ አጠቃላይ ጉባኤ የሰበካ ጉባዔያት ጠንካራና ደካማ ጎን ይገመገማል፤ ከጊዜው ጋር እየተገናዘቡ የሰበካ ጉባዔውን ሂደት የሚያጠናክሩ ውሳኔዎች፣ መመሪያዎችና ዕቅዶች እየወጡ በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርምረው ከጸደቁ በኋላ ሥራ ላይ ይውላሉ።

በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥና በውጭ አገሮች:-

- ከ፴፫ ሺ ያላነሱ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት – ፬ መቶ ፲፪ ሺ ፬፻፲፮ ካህናት
- ፵ ሚሊዮን አርባ ሚሊዮን ምእመናን በቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት በሰበካ ጉባዔ ተደራጅተው ይገኛሉ።

www.ethiopianorthodox.org

# የሰንበት ትምህርት ቤት

የነገይቱን ቤተ ክርስቲያን ተረካቢዎች ወጣቶች እንደመሆናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽህፈት ቤት በማዕከላዊ ደረጃ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ አቋቁማ በመላው ኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ወጣቶችን በሰንበት ትምህርት ቤት በማደራጀት ላይ ትገኛለች። ቅዱስ ሲኖዶስ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የቤተ ክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት ተከትለው የሚመሩበት መተዳደሪያ ደንብ አውጥቷል። በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ከሚመረጡት የሰበካ ጉባኤ አባላትም አንዱ ክፍል የሰንበት ትምህርት ቤት ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ለወጣቶቹ መንፈሳዊ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራንን ትመድባለች፣ የሚማሩባቸው መጻሕፍትን አቅም በፈቀደ መጠን እያዘጋጀች ታሠራጫለች የመሰብሰቢያና የመማሪያ አዳራሾችና አብያተ መጻሕፍት እንዲሠሩላቸው ብርቱ ጥረት ታደርጋለች። በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት በደረጃቸው እንዲሳተፉ ታደርጋለች። በመደባቸው ለሚያንቀሳቅሱት መንፈሳዊ ተግባር የሚረዳ በጀት ከሰበካ ጉባኤው መድባ እንዲሠሩ ታደርጋለች። ወጣቶችም በበኩላቸው ከመደበኞቹ ካህናት ጎን ተሠልፈው በመዝሙር፣ በትምህርተ ወንጌል በቅዳሴ ተሰጥዎና በጠቅላላው መንፈሳዊ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን ይረዳሉ። በተለይ በገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ጎልቶ የሚታየው የወጣቶቹ አገልግሎት ነው። ድራማዎችን በማሳየት መዝሙራትን በመድረስና በካሴት እያስቀረጹ በማሠራጨት፣ የሃይማኖት መጻሕፍትን ጋዜጦችና መጽሔቶችን እያዘጋጁ በማሳተም እንደ ቅዱስ ቁርባንና የተክሊል ጋብቻ የመሳሰሉትን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ራሳቸው በተግባር በመተርጐም ለቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ሕይወት መልካም አርአያነትን እያተረፉ ናቸው።

የገቢ ምንጭ በመፍጠር የሰንበት ትምህርት ቤቶቻቸውን ያስፋፋሉ ያጠናክራሉ። በየገዳማቱና ታሪካዊ ሥፍራዎች ጉብኝት በማድረግ ታሪካቸውን ለማወቅ ጥረት ያደርጋሉ። ምዕመናንን በማስተባበር ለየአካባቢያቸው ችግረኞች ከዕለት ጉርስ እስከ ዓመት ልብስ ርዳታ በማድረግ የምግባረ ሠናይ ሥራ ያከናውናሉ። አብያተ ክርስቲያናት በሚታነጹበትና በሚታደሱበት ከምእመናን ጋር እየተሠለፉ ከፍተኛ

www.ethiopianorthodox.org

አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ለሚንቀሳቀሱት የራስ አገዝ የልማት ተቋሞችም የሚያደርጉት እገዛ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

## ትምህርት

ጥንታዊቷና ብሔራዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ምንጭ ሆና የኖረች ቤተ ክርስቲያን ናት የቤተ ክርስቲያን መሠረት መንፈሳዊ ትምህርት እንደመሆኑ መጠን የቤተ ክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤቶች በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ተዘርግተው ኖረዋል። በገጠርም ሆነ በከተማ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ያልተቋቋመበት ቤተ ክርስቲያን አይገኝም። ከጥንት ጀምሮ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደበቱን የሚፈታው መሠረታዊ የቋንቋና የሥነ ጽሕፈት ዕውቀት የሚያገኘው ከዚች ቤተ ክርስቲያን ነው።

ዘመናዊው ትምህርት በሀገሪቱ እስከተዘረጋበት ቅርብ ጊዜ ድረስ ጠቅላላው የትምህርት ቁልፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ እጅ የተያዘ ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታውያን የአብነት ትምህርት ቤቶች ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱ ብዙ ሊቃውንትን ሲያበረክቱ ኖረዋል ሕዝበ ክርስቲያኑም ከአባቶች የወረሰውን ባህላዊ ትውፊት በመከተል ለመንፈሳዊው ትምህርት መምህራንና ደቀ መዛሙርት የኑሮ ድጋፍ በመስጠት ለሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መበራከት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሲያበረክት ኖሮአል።

ይህን ጥንታዊና መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በቆየው መልኩ በልመና ቁራሽ ለመቀጠል ወቅቱ እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ለመምህራንና ደቀመዛሙርቶቻቸው ድጎማ በመስጠት ትምህርቱ እንዳይቋረጥ አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች በተለይ በአዲስ አበባ አድባራትና በሌሎችም አህጉረ ስብከት መንፈሳዊ የአዳሪ ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋትና በማጠናከር ትምህርቱ በስፋት እንዲቀጥል በመደረግ ላይ ነው።

በቀድሞ መንግሥት ተወስዶ የነበረው መንፈሳዊ ኮሌጅ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ ትጋትና ጥረት ተመልሶ ለዓመታት ተቋርጦ የነበረው ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርትና የክህነት ሥልጠና

www.ethiopianorthodox.org

ቀጥሏል ቁጥራቸው በርከት ያለ ደቀ መዛሙርት ትምህርታቸውን በመከታተል በሠርተፊኬት፣ በዲፕሎማና በዲግሪ እየተመረጡ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው። በዚሁ ኮሌጅና በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በዲግሪና ዲፕሎማ ከሚሰጠው መደበኛ ትምህርት በተጨማሪ ለየአህጉረ ስብከት ካህናትና የልዩ ልዩ አገልግሎት ዘርፍ የሠራተኞች የሚሰጠው አጭርና የረጅም ጊዜ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ቤተ ክርስቲያኒቱንና ኅብረተሰቡን እጅግ እየጠቀመ ነው። የምእመናን ልጆች መንፈሳዊውን ዘመናዊውን ትምህርት የሚማሩባቸው ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች በየአድባራቱ በብዛት እየተሠሩ አገልግሎት በመስጠት ላይ ስለሆኑ የመንፈሳዊው ትምህርት መርሐ ግብር ከምን ጊዜውም በበለጠ በምልዓትና በስፋት እየተካሄደ ነው።

## መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት

የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ተልእኮ ለመላው የሰው ዘር መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት መስጠት ነው።

ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰቡ መካከል በመገኘት የሃይማኖት፣ የዘርና የጐሳ ልዩነት ሳታደርግ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ስትሰጥ ኖራለች። ለሕዝቡ የተሟላ ኑሮና ብልጽግና በሚዘረጉ የልማት አውታሮችም የበኩሉዋን አስተዋጽኦ ስታደረግ የኖረች ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ናት። አሁንም ይህንኑ ተልእኮዋን በስፋት በመቀጠል በአህጉር ደረጃ ከመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት በዓለም አቀፍ ደረጃም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጋር በመተባበር ሌሎች የሰብአዊና የምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን በማስተባበር በልማትና በርዳታ ሥራ የበኩሉዋን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ትገኛለች። በዚሁ ዓላማዋም ባለፉት ተከታታይ ዐሥርት ዓመታት በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች በተከሠቱ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች በተቸገረው ሕዝብ መካከል እየተገኘች የርዳታ ተግባር ስታከናውን ቆይታለች። በመልሶ ማቋቋምና ዘላቂ የልማት ዕቅዶችም ትምህርት ቤቶችንና ክሊኒኮችን፣ መንገዶችንና ድልድዮችን፣ የችግኝ ጣቢያዎችንና የዛፍ ተከላ መርሐ ግብሮችን፣ የከብት ርባታዎችንና ልዩ ልዩ የጎጆ ኢንዱስትሪዎችን፣ የጉድጓድ ውሃ

www.ethiopianorthodox.org

ቁፋሮዎችንና የምንጭ ማጐልበት ሥራዎችን የመሳሰሉትን በማካሄድ የሚጠበቅባትን ማኅበራዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ትገኛለች። ራስ አገዝ የሆኑ የልማት ተግባራትም በየአህጉረ ስብከቱ በስፋት በመከናወን ላይ ይገኛሉ።

ከዚህም ሁሉ ጋር በተለያዩ ምክንያቶች ወላጅ አልባ የሆኑ ዕጓለ ማውታና የችግረኞች ልጆችን በማሰባሰብ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ እየሰጠች በማስተማር አሳድጋ አያሌ ወጣቶችን ለቁም ነገር አብቅታለች በዚሁ መልክ ያለው አገልግሎት አሁንም በተሻለ መልኩ በመቀጠል ላይ ይገኛል።

ከተባበሩት መንግሥታትና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጋር ባለው የማኅበራዊና ሰብአዊ አገልግሎት ቅንጅትም የስደተኞች አገልግሎት ኃላፊነትን ወስዳ ባቋቋመችው ጽህፈት ቤት በአሁኑ ጊዜ ከአፍሪካና ከዓለም ዙሪያ የተፈናቀሉ ስደተኞችን በየመልኩ በመርዳትና በማስተናገድ ላይ ትገኛለች።

## ሕንጻ መንበረ ፓትርያርክ

ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜም ቢሆን ያለፈተና አሁን ካለችበት ደረጃ አልደረሰችም በረዥሙ የታሪክ ጉዞዋ አያሌ ፈተናዎችን አሳልፋለች። በጥንታዊነቷ በታሪካዊነቷ በብሔራዊነቷ ብዙ መናፍቃንና ቢጽ ሐሳውያን ይቀናቀኑአታል በየወቅቱም ይፈታተኑአታል። በየዘመናቱ በሚደረጉ የመንግሥታትና የሥርዓት ለውጦችም በህልውናዋ ላይ ችግሮችና ፈተናዎች ሳይገጥሟት ቀርተው አያውቁም ዛሬም ቢሆን ከችግሮችና ፈተናዎች ሙሉ በሙሉ ነፃ ነች ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ በጽኑ አለት ላይ የተመሠረተች ስለሆነች በየጊዜው የሚነፍሰው ነፋስ ሁሉ ሊያናውጣት አልቻለም ይልቁንም ችግሩና ፈተናው ሁሉ ይበልጥ እንድትጠናከርና እንድትስፋፋ ረድቷታል።

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም የተከታዩቿ ብዛት እየጨመረ በመሄዱ በዚያው መጠንም የአብያተ ክርስቲያናት ቁጥር እያደገ በመምጣቱ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት በብዛት በመታነጽ ላይ ናቸው። እድሳትና ጥገና እየተደረገላቸው ያሉ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራትም በርካታዎች ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ይህን በመሰለው የዕድገትና የመሻሻል ሂደት ውስጥ በተለይ በአሁኑ ጊዜ እጅግ አስደናቂ ሆኖ የሚታየው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ከፍተኛ ጥረት፤ በአብያተ ክርስቲያናትና በምእመናን ትብብር የተሠራው አዲስ ሕንጻ መንበረ ፓትርያርክ ነው። ይህ ሕንጻ ጥንታውያንና ታሪካውያን የሆኑትን የአክሱምን የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናትና የፋሲልን ቤተ መንግሥት አሠራር የያዘ በመሆኑ ጥንታዊውንና ባህላዊውን የኢትዮጵያውያን የሥነ ሕንጻ ፈጠራና ችሎታ የሚያንጸባርቅ ነው። ሕንጻው የተሠራበት ዐቢይ ምክንያት:- ቀደም ሲል የነበረው ሕንጻ መንበረ ፓትርያርክ ለመንበረ ፓትርያርክ የሚመጥን ባለመሆኑ— ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታዊነትና ታላቅነት አኳያ ዓለም አቀፍ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችንና እንግዶችን ለማስተናገድ የማይችል በመሆኑ:-

በቅርጹና በአሠራሩ ከጥንት ጀምሮ በሀገራችን ሲያያዝ የመጣውን ታሪካዊ የሕንጻ አሠራር ጥበብ አጉልቶ የማያሳይ በመሆኑ ነው።

አዲሱ ሕንጻ መንበረ ፓትርያርክ ግን እነዚህን ሁሉ አገልግሎቶች አሟልቶ ለመስጠት የተመቻቸ ሆኖ ተሠርቷል። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ መንበርነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዕድገት ጐዳና የምታደርገውን ርምጃ አጉልቶ የሚያሳይ ነው። «ሕግ ይወጽእ እምጽዮን» እንደተባለው ሕገ ቤተ ክርስቲያን የሚወጣበት የእምነትና የሥርዓት ውሳኔዎችና መመሪያዎች የሚተላለፉበት ይኸው ሕንጻ መንበረ ፓትርያርክ በመሆኑ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ነው።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ያለፉትን አበው ታሪክ ለትውልድ ለማስተላለፍ በምታደርገው ጥረት ባለፈው ሥርዓት በግፍ የተገደሉት የሁለተኛው ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሐውልትና ቤተ መዘክር እንዲሠራ አድርጋለች። ይህም ሐውልትና ቤተ መዘክር ሊሠራ የቻለው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ልዩ ጥረት ነው።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በመላ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤን መሠረት የጣሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ የውጭ

www.ethiopianorthodox.org

ላይ የሚደርሱ ችግሮችን ለመከላከልና ለማስወገድ ሰብአዊና መንፈሳዊ አገልግሎት ትሰጣለች።

ከዓለም አቀፍ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ለሰው ልጆች ማኅበራዊ ሕይወት ሰላምና ደኅንነት ከቆሙ መራሕያነ መንግሥታት ጋር በየጊዜው የጉብኝት ልውውጥ ታደርጋለች።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ርእስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት በቅርቡ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በኢየሩሳሌም፣ በአሜሪካ፣ በካሪቢያን አገሮች በኢንግላንድ፣ በሮም፣ በአቴንስ፣ በራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ በአርማንያ እና በቱርክ ጉብኝት አድርገዋል። ከአብያተ ክርስቲያናቱና ከየሀገሩ መንግሥታት መሪዎች ጋር ስለ ሀገራችን ሕዝብ ታሪክና ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊነት በሠፊው አስረድተዋል።

በዚሁ አንፃር የአብያተ ክርስቲያናትና የተለያዩ አገሮች መንግሥታት መሪዎች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሪዎችና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ አባላት ወደ ሀገራችን እየመጡ በተለያዩ ጊዜያት ጉብኝት አድርገዋል። ስለሀገራችን ታሪክና ሥልጣኔ፣ ስለቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊነትና ሥርዓተ አምልኮ በሠፊው ተረድተዋል። ከነዚህም ታላላቅ የመንግሥታትና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች መካከል የጀርመን ፌዴራል ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት፣ የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እንዲሁም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊና የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ ዋና ፀሐፊ በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ቤተ ክርስቲያናችንን ጎብኝተዋል። ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖትና ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጋር:-

- ስለ ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ግንኙነት መጠናከር፣
- ስለ ዓለም ሰላምና የሰው ልጆች ደህንነት
- በማኅበረሰብ ችግሮች ላይ በጋራ ስለ መሥራት በሠፊው ተወያይተዋል።

www.ethiopianorthodox.org